በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የጎንደር ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች

ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የጎንደር ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. የኢትዮጵያ የፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 64 የፍትሐብሔር እርምጃ በሚለው ንኡስ አንቀፅ 1እና 2 ላይ ማናቸውንም የገንዘብና የንብረት ጉድለት ለማስመለስ የሚያስችል የሕግ እርምጃ የፍትሕ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት መወሰድ አለበት፡፡ ሚኒስትሩ በአዋጅ አንቀጽ 13 መሰረት የመንግስት መ/ቤት ክሱን እንዲያቆም በተለይ ካልፈቀደ በስተቀር የመንግስት ሰራተኛ ተጠያቂ የሆነበትን ያጎደለውን ንብረት ወይም ገንዘብ መመለስ እንዳለበት የሚያዝ ቢሆንም፣ ከ2008 በጀት ዓመት ለ2009 በጀት ዓመት የዞረ ጥሬ ገንዘብ በዩኒቨርስቲው ሆስፒታል ብር 29,947.15 እና በዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 905.16፣ በድምሩ ብር 30,852.31 በጥሬ ገንዘብ ጉድለት (በሂሳብ መደብ 4202) የተመዘገበ ቢሆንም እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30/2009) ድረስ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

2. በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል ክፍል 6 አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነጻ የሆነ የገቢ መጠን ከገቢ ግብር ነጻ

እንደሆነ፣ ተደራራቢ ታክስን ለማስቀረት በኢትዮጵያ መንግሥት እና በህንድ መንግሥት መካከል በተደረገ ሥምምነት አንቀጽ 20 ፕሮፌሰሮች፣ መምህራኖች እና ተመራማሪዎች በሚለዉ ሥር በኢትዮጵያ እዉቅና በተሰጠዉ የትምህርት ተቋም ዉስጥ በሙያዉ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ተመራማሪ /አስተማሪ ኢትዮጵያ ዉስጥ በሰጠው አገልግሎት ከሚያገኘው ገቢ ላይ ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ቀን ጀምሮ ከሁለት አመት ላልበለጠ ጊዜ ከግብር ነፃ መሆኑ የተጠቀሰ እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በ01/12/09 በቁጥር ተ/ደ/ቀ/1/277 በተጻፈ ማብራሪያ ደግሞ ከአሜሪካና ከእንግሊዝ የሚመጡ መምህራን ኢትዮጵያ ውስጥ በሙያቸው በሰጡት አገልግሎት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ተገቢውን ግብር መክፈል ያለባቸው ሲሆን ከፈረንሳይና ከህንድ የሚመጡት ግን በስምምነቱ መሠረት የማስተማር/የምርምር አገልግሎቱን ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ቀን አንስቶ ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከግብር ነጻ መሆናቸው የተገለጸ ቢሆንም ሁለት ዓመት ያለፋቸው 28 የህንድ መምህራን በበጀት ዓመቱ ከተከፈላቸው ደመወዝ ላይ ብር 6,054,599.28 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፣

3. የፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 በመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጭዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም፣በዩኒቨርሲቲው ለአንዳንድ ግዥዎች በድምሩ ብር 211,237.80 የተከፈለ ሲሆን ተገቢው የወጪ የሰነድ ማስረጃ አለመኖሩ/አለመቅረቡ/፣
4. ለተለያዩ ዕቃዎች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) በዋናው ግቢ ተከፍሎ በድምሩ ብር 1,888,842.98 በወጪ የተመዘገበው ሲሆን የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፣
5. በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም በአጼ ቴዎድሮስ ካምፓስ ብር 43,900.00፣ በጤና ሳይንስና ህክምና ኮሌጅ ብር 224,000.00፣ በማራኪ ግቢ ብር 8,000.00 እና በመለስ ዜናዊ ግቢ ብር 66,000.00፣ በጠቅላላ ድምሩ ብር 341,900.00 በመንግሥት የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር ከመደበኛ በጀት ለክብር ክፍያ (Honorarium) መከፈሉ፣
6. በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ማንኛውም የመንግስት ተቋም በተቋሙ ፕሬዚዳንት ጥያቄና በቦርዱ ውሳኔ የገቢ ማስገኛ

ድርጅት ሊያቋቁም እንደሚችል እና ድርጅቱ የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ህጉ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት የሚሰራ መሆኑ የተደነገገ ቢሆንም፣ ዩኒቨርሲቲው በህጋዊ መንገድ ያቋቋማቸው የጃንተከል ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ እና የብሩህ ሆቴልና መስተንግዶ ኢንተርፕራይዝ የራሳቸውን ወጪ በራሳቸው ገቢ እንዲሸፍኑ ማድረግ ሲገባ፣በዓጼ ቴዎድሮስ ግቢ ለብሩህ ሆቴልና መስተንግዶ ኢንተርፕራይዝ ሠራተኞች ደመወዝ ብር **501,073.00** እና በማራኪ ግቢ ለጃንተከል ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ ሰራተኞች ደመወዝ ብር **211,303.34**፣በድምሩ ብር **712,376.34** በበጀት ዓመቱ ከመደበኛ በጀት ለደመወዝ የተከፈለ መሆኑ፣

7. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር **47,163,331.14** ሲሆን ከዚህ ውስጥ በዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል የሰኔ 30/2009 ዓ.ም የተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገቢያ (አይ ቤክስ) ላይ የሚታየው በሂሳብ መደብ 4201 በልዩ ልዩ የተሰብሳቢ ሂሳቦች ብር 8,560.86 እና በሂሳብ መደብ 4202 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ብር 29,947.15፣ በድምሩ ብር 38,508.01 ከማን እንደሚሰበሰብ ለማወቅ ይቻል ዘንድ በእያንዳንዱ ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተ እና ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
8. **በመለስ ዜናዊ ካምፓስ** ሰኔ 30/2009 ዓ.ም በተከፋይ ሂሳብ መመዝገቢያ (አይ ቤክስ) ላይ በሂሳብ መደብ 5002 በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች ለተያዘ ብር 692,724.91፣ እና

   በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ተከፋይ ሂሳብ መመዝገቢያ (አይ ቤክስ) ላይ በሂሳብ መደብ 5002 በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች ለተያዘ ብር 16,711.22፣

   በድምሩ ብር **709,436.13** ብር ለማን እንደሚከፈል ለማወቅ የሚያስችል በያንዳንዱ ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተ መሆኑ፣
9. ከመደበኛ በጀት ብር 8,276,364.62 እና ከካፒታል በጀት ብር 337,902.98፣ በድምሩ ብር 8,614,267.60 ከተፈቀደው በጀት በላይ ሥራ ላይ መዋሉ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

1. በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.1 በአዋጅና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ

በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው የተገለጸ የዩንቨርሲቲዉን የሥራ ክፍሎች ለመሸለም ከትግስትና ተስፋየ ገጸበረከትና የዕደጥበብ መሸጫ የብር 221,353.30 ክሪስታልና ሜዳልያ ግዥ ያለምንም ውድድር የተፈጸመ መሆኑ፣

2. ሰኔ/2002 ባወጣው የፌዴራል መንግስት የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 3 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የተለያዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ከአቀራቢዎች/ከስራ ተቋራጮች/ ጋር የተደረገውን የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ እንደሚኖርባቸው የተገጸ ቢሆንም፣ የሥራ ተቋራጮች 4 ግንባታዎችን በውላቸው መሰረት ማጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ21 እስከ 187 ቀናት ያዘገዩ እና በተጨማሪም ከላይ ከተጠቀሱ ግንባታዎች ውስጥ ሎት-19 ፐብሊክ ሄልዝ ግንባታ የሚገነባው ክራፍት ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ ሥራ ተቋራጭ ግንባታውን እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ለ187 ቀናት ከማዘግየቱ በተጨማሪ 181 ቀናት የፀደቀ የውል ማራዘሚያ ጊዜ ተሰጥቶት እንደነበረ፣

3. ከመደበኛ በጀት ብር 16,877,890.26 ከየሂሳብ መደቡ ከ10% በላይ ሥራ ላይ አለመዋሉ፣

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

1. **ንብረት፣**

1.1 **አላቂና ቋሚ ዕቃዎች፣**

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በእቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ፡-

- በንብረት መጠበቂያ መጋዘኖች ውስጥ የሚገኙት የተወሰኑ እቃዎች በዓይነት፣ በባህሪይና በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በሥርዓት ያልተቀመጡ መሆኑ፣
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ በዕርዳታ ከCentre for International Unique in Ethiopia የተገኙ የህክምና ዕቃዎች በዩኒቨርሰቲው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) የተዘጋጀላቸው ቢሆንም ዋጋቸው ያልተጠቀሰ መሆኑ (ለምሳሌ፡- ሞ/19 ቁጥር 814351-814400)፣
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጡ አዳዲስ ንብረቶች፣ ለምሳሌ፡- 14 የኮንፈረንስ ቴብል፣ 4 የገንዘብ ካዝናዎች፣ 7 ሲፓፕ የህክምና ማሽን፣ 81 ለብዙ ጊዜ የቆዩ

የተለያዩ ሰሌዳዎች፣ 16 ኢንፌንታ ራዲያተርና እንኩቤተር፣ 86 ዌይት ስኬል (ሚዛን)፣ የመሪ ዘይት፣ 528 የቧንባ ዕቃዎች መኖራቸው፣

- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የፕሪንተር እና የፎቶ ኮፒ ቀለሞች፣ ላርጎ ሳሙና እና የተለያዩ የደምብ ልብሶች ክፍሉን አጣብበው መቀመጣቸው፣
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ አራት ምን እንደያዙ ያልታወቀ ሲሊንደሮች አሲድ መያዙን አለመያዙን ያልታወቃ መሆኑንና ከንብረት ጋር ስቶር ዉስጥ ለዓመታት ተቀምጦ መገኘቱ፤
- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ አገልግሎት አይሰጡም ተብሎ የተመለሱ እንደ ዩፒኤስ ብዛት 202፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን ብዛት 30፣ እስቴትስኮፕ ብዛት 165፣ የብረት ወንበር ብዛት 7፣ የተለያዩ ሞባይሎች ብዛት 09፣ ቶሽባ ላፕ ቶፕ ብዛት 107፣ ኤችፒ ላፕ ቶፕ ብዛት 28፣ ታይፕራይተር ብዛት 29፣ ዴል ኮምፒዩተር ሲስተም ብዛት 128፣ ኤችፒ ሲስተም ብዛት 40፣ ኤችፒ ሞኒተር ሲስተም ብዛት 90፣ ኤችፒ ፕሪንተር ብዛት 50፣ የምግብ ቤት ማሽን ብዛት 15፣ የተለያዩ የመኪና ጎማዎችና ስፐር ፓርቶች፣ እስፖንጅ ፍራሾች ብዛት 818፣ ማርቴ በጣሳ ብዛት 1702፣ ቁጥራቸዉ የማይታወቁ ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የጣዉላ ሎከሮች እና የተለያዩ ብረታ ብረቶች (ወደ ስቴዲዮም አከባቢ)፣ ሚክሲድ ፎሲት ብዛት 152፣ የብሉኬት ማፍጫ የብረት ብዛት 196 ያሉ በርካታ ንብረቶች ተከማችተው የተቀመጡ መሆናቸው፤ ታውቋል፡፡

1.2 <u>ተሽከርካሪ መኪናዎች</u>፣

- በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ዓ.ም ክፍል ሁለት አንቀፅ 6/1 የመንግሥት መ/ቤት በግዥ፣ በስጦታ፣ በዝውውር…ወዘተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ መኪና የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ ቢያንስ መሠራታዊ መረጃዎችን መዝግቦ መያዝ እንዳለበት፣
- በዚሁ መመሪያ ክፍል 3 አንቀጽ 9/1 እና 2 ደግሞ መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተል እና መዝግቦ ለመያዝ እንዲረዳቸው የተሽከርካሪዎች የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸውና እያንዳንዱ ተሸከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም፣
  - የ4 የተለያዩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መከታተያ የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ የማይሰራ መሆኑና ተሽከርካሪዎቹ በሄዱበት ኪ/ሜ ተገምቶ ነዳጅ የሚሞላላቸው መሆኑ፣

- 4 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ፣

2. በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፤ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች የማደራጀትና በቂ የትምህርት ዝግጅትና አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያካበተ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ የመመደብ የመ/ቤት የበላይ ኃላፊ ኃላፊነት እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በክፍሉ ዘጠኝ (9) ክፍት የሥራ መደብ የነበረ መሆኑ፣

ከሰላምታ ጋር

ፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ

የ2009 ኦዲት ሂሳብ ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የ**ጎንደር** ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፤

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፤ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ **በጎንደር** ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡ የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው

ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>**የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ፤**</u>

1.1 <u>**ግኝት፤**</u>

የኢትዮጵያ የፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 64 የፍትሐብሔር እርምጃ በሚለው ንኡስ አንቀፅ 1እና 2 ላይ ማናቸውንም የገንዘብና የንብረት ጉድለት ለማስመለስ የሚያስችል የሕግ እርምጃ የፍትሕ ሚኒስቴር በሚወታው መመሪያ መሰረት መወሰድ አለበት፡፡ ሚኒስትሩ በአዋጅ አንቀጽ 13 መሰረት የመንግስት መ/ቤት ክሱን እንዲያቆም በተሌ ካልፈቀደ በስተቀር የመንግስት ሰራተኛ ተጠያቂ የሆነበትን ያጎደለውን ንብረት ወይም ገንዘብ መመለስ እ”ÇKuƒ የሚያዝ ቢሆንም፣

ከ2008 በጀት ዓመት ለ2009 በጀት ዓመት የዞረ ጥሬ ገንዘብ በዩኒቨርስቲው ሆስፒታል ብር 29,947.15 እና በዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 905.16፣ በድምሩ ብር 30,852.31 በጥሬ ገንዘብ ጉድለት (በሂሳብ መደብ 4202) የተመዘገበ ቢሆንም እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30/2009) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.2 <u>***ሥጋት፣***</u>

የዩኒቨርሲቲው የጥሬ ገንዘብ አያያዝ በደንብና መመሪያው መሰረት ተግባራዊ ካልተደረገ የህግ ጥሰትን ከማስከተሉም በላይ የመንግስት ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.3 <u>**የማሻሻያ ሃሳብ፡-**</u>

የዩኒቨርሲቲው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በልዩነት የታየው ብር 30,852.31 ለዩኒቨርስቲው ገቢ ተደርጎ የገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት ይገባል፡፡

1.4 <u>**የስራ አመራሩ ምላሽ፣**</u>

የሥራ አመራሩ፣በሆስፒታል ገቢ የሚታየዉ ብር 29,947.15 በግቢዉ በተከናወነዉ የካዝና ዘረፋ ምክንያት ጉዳዩ በሕግ ተይዞ የቆየ ሲሆን በወቅቱ ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ሠራተኛ

በዲሲፕሊን ዉሳኔ ከደረጃ ዝቅ ብለዉ እንዲሠሩ ተወስኖ ዉሳኔዉ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፤ የጥሬ ገንዘቡን ጉድለት ለማስተካት ግን ጉዳዩ በሕግ የተያዘ ስለሆነ ዉሳኔ ሲደርስ ተፈጻሚ የሚደረግ መሆኑን፣

- በሕክምናና ጤና ሳይንስ ግቢ ታይቶ የነበረዉ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት በአቶ ኃይሉ ተክሉ ብር 905.51 (ዘጠኝ መቶ አምስት ብር ከሃምሳ አንድ ሳንቲም) በጉድለት የሚታይ ሲሆን በወቅቱ ለማኔጅመንቱ አሳውቆ ውሳኔ እንዲሰጥበትና እንዲሰረዝ በዉስጥ ኦዲት ምርመራ በማከናወን የዩኒቨርሲቲዉ ሥራ አመራር ካዉንስል ዉሳኔ አሳልፎበት የቆየ ስለሆነ የማስተካከያ ምዝገባ እንዲከናወን መደረጉን በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የሚተካውን በማስተካት እና በምዝገባ ማስተካከያ የሚስተካከለውን በማስተካከል ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2. <u>ከህንድ ሀገር መምህራን ደመወዝ ላይ የሥራ ግብር ያልተቀነሰ ስለመሆኑ</u>፣

2.1 <u>ግኝት</u>፣

በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል ክፍል 6 አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነጻ የሆነ የገቢ መጠን ከገቢ ግብር ነጻ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡

በተጨማሪም ተደራራቢ ታክስን ለማስቀረት በኢትዮጵያ መንግሥት እና በህንድ መንግሥት መካከል የተደረገ ሥምምነት ሲታይ በስምምነቱ አንቀጽ 20 ፕሮፌሰሮች፣ መምህራኖች እና ተመራማሪዎች በሚለዉ ሥር በኢትዮጵያ እዉቅና በተሰጠዉ የትምህርት ተቋም ዉስጥ በሙያዉ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ተመራማሪ /አስተማሪ ኢትዮጵያ ዉስጥ በሰጠው አገልግሎት ከሚያገኘው ገቢ ላይ ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ቀን ጀምሮ ከሁለት አመት ላልበለጠ ጊዜ ከግብር ነፃ መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በ01/12/09 በቁጥር ተ/ደ/ቀ/1/277 በተጻፈ ማብራሪያ ደግሞ ከአሜሪካና ከእንግሊዝ የሚመጡ መምህራን ኢትዮጵያ ውስጥ በሙያቸው በሰጡት አገልግሎት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ተገቢውን ግብር መክፈል ያለባቸው ሲሆን ከፈረንሳይና ከህንድ የሚመጡት ግን በስምምነቱ መሠረት የማስተማር/የምርምር አገልግሎቱን ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ቀን አንስቶ ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከግብር ነጻ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

በዚህ መሠረት ሁለት አመት ያለፋቸዉ የህንድ መምህራን ግብር እንደሚከፈሉ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ሁለት ዓመት ያለፋቸው 28 የህንድ መምህራን በበጀት ዓመቱ ከተከፈላቸው ደመወዝ ላይ ብር 6,054,599.28 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 1 ተይዟል፡፡)

2.2 ሥጋት፣

- ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት ገንዘብ ለግለሰቦች መሰጠቱ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል፡፡ መንግስት ማግኘት የነበረበትን ገቢ እንዳያገኝም ያደርጋል፡፡

2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲው የሥራ ግብሩ ካልተሰበሰበባቸው ግለሰቦች ላይ ገንዘቡን ተመላሽ ሊያደርግ እና ተመሳሳይ ክፍያዎች ካሉ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ ለዉጭ ሃገር መምህራን በአጠቃላይ ታክስ መከፈል ያለበት በመሆኑ ከህንድ አገር ዉጭ የሚገኙ ሌሎች መምህራንን ታክስ በማስከፈል ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ የህንድ መምህራንን በተመለከተ ደግሞ እንደ አዉሮፓ አቆጣጠር May 25 2011 በኢትዮጵያ እና በሕንድ አገሮች መካከል የሁለትዮሽ ስምምነት አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከሕንድ አገር በሚመጡ እና በመንግሥት የትምህርት ተቋማት የሚሠሩ መምህራን ዉል ለገቡበት የማስተማር ሥራ ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከሥራ ግብር ነጻ እንደሚሆኑ ስለሚገልጽ በዩኒቨርሲቲው የህንድ መምህራን የሚቀጠሩበት ረዥም ጊዜ 2 ዓመት ሲሆን፣ መምህራን የኮንትራት ጊዜያቸዉ ካለቀ በኋላ ግን እንደገና የሚቀጠሩበት ሁኔታ ስላለ የቅጥር ዉሉን መነሻ በማድረግ ታክስ ሳይቀነስባቸዉ የቆየ መሆኑን እና የኮንትራት ዉላቸዉ በ2 ዓመት ጊዜ ሲጠናቀቅ ወደ ሃገራቸዉ ከተመለሱ በኋላ እንደ ማንኛዉም መምህር ተወዳድረዉ ሲመረጡ እንደገና በአዲስ ዉል ለ2 ዓመታት የሚቀጠሩ መሆናቸዉን ገልጸው፤ እንደገና በአዲስ ዉል የሚቀጠሩ የህንድ መምህራን ደመወዝ ላይ ታክስ ሊቀነስ የሚገባ ከሆነ ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተጠይቆ በሚሰጣቸው ምላሽ መሠረት ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

2.4 የኦዲተሩ አስተያየት፣

መምህራኑ ያገለገሉት በኮንትራት ቅጥር ነው ቢባልም ያገለገሉት በመመሪያው ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ ስለሆነ ግብሩ ከደመወዛቸው መቀነስ ነበረበት፡፡ በመሆኑም

በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት ዩኒቨርሲቲው የሥራ ግብሩ ካልተሰበሰበባቸው ግለሰቦች ላይ ገንዘቡን ተመላሽ ሊያደርግ እና ሌሎች ተመሳሳይ ክፍያዎች ካሉ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

የወጪ ሂሳብ፤

ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋለው የወጪ ሂሳብ በፌዴራል መንግስት ታምኖበት በወጡ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን እንዲሁም ለማንኛውም ክፍያ የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች የቀረቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጪ፤

3.1.1 ግኝት፤

የፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 በመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጭዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም ግን በዩኒቨርሲቲው ለአንዳንድ ግዥዎችና

ቀን	የባንክ ወጪ ማስ. ቁጥር	የሂሣብ መደብ	ገንዘቡን የተቀበለው እና የወጪው ምክንያት	የገንዘቡ ልክ
02/8/09	692818	6412	ለሀገሬ ሚዲያ ኮሚኒኬሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ለድጋፍ የተከፈለ (**ዋናው ግቢ**)	60,000.00
07/9/09	688326	6216	ለሙሐመድ አብድራህማን ዳቦ አቅራቢ ለዳቦ ግዥ የተከፈለ (**መለስ ዜናዊ ግቢ**)	151,237.80
			ድምር	**211,237.80**

በድምሩ ብር 211,237.80 ክፍያ ሲፈጸም ተገቢው የወጪ የሰነድ ማስረጃ አለመኖሩ/አለመቅረቡ/ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3.1.2 ስጋት፤

የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጪ ለተቋሙ አገልግሎት የዋለ መሆኑን አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

የወጪ ሂሣብ በተሟላ ማስረጃ መደገፍ ስለሚገባው የክፍያ ደረሰኝ ላልቀረበላቸው የወጪ ሂሣቦች ደረሰኞቹ እንዲቀርቡ የተቋሙ አመራር ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

የስራ አመራሩ፣

- ከሃገሬ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከመሐመድ አብዱህማን ሊሰበሰብ የሚገባዉ ደረሰኝ ተሰብስቦ ከሰነዱ ጋር መያያዙን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ሊሰበሰብ የሚገባዉ ደረሰኝ ተሰብስቦ ከሰነዱ ጋር ተያይዟል ለተባለውም የደረሰኞቹ ኮፒ ከምላሹ ጋር አልቀረቡም፡፡ ስለሆነም በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

3.2 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ ሂሳብ፣

3.2.1 ግኝት፣

በፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጭዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ በዚሁ መሠረት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ለተፈፀመባቸው ግዥዎች ተገቢው ደረሰኝ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለተለያዩ ዕቃዎች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው፣

ቀን	የባንክ ወጪ ማሰ. ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የገንዘቡ ልክ	የወጪው ምክንያት	የተቀባይ ድርጅት ስም
30/05/09	690036	6314	1,538,300.00	የፈርኒቸር ግዥ	ደጀኔ ለማ የቤትና የቢሮ እቃዎች አስመጪና አምራች
10/09/09	694313	6212	350,542.98	አላቂ ዕቃ ግዥ 9 ፋይል ቦክስ)	ብራይት ስቴሺነሪይና ኮምፒተር
		ድምር	**1,888,842.98**		

በድምሩ ለብር 1,888,842.98 የዋናው ገቢ የወጪ ሂሳብ የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3.2.2 ስጋት፣

ድርጊቱ የመንግሥትን ህግና ደንብ ሳይከተሉ የሚሰሩ አቅራቢዎችን የሚያበረታታ እና ገቢያቸውን በመደበቅ የሚጠበቅባቸውን ግብር በአግባቡ እንዳይከፍሉ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

3.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ

በዱቤ ሽያጭ ለተመዘገበው የወጪ ሂሳብ የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ እንዲቀርብ እንዲደረግና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

3.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

የሥራ አመራሩ፣

በዱቤ ደረሰኝ የተወራረዱ የተባሉት፣ ክፍያዎች የዱቤ ደረሰኝ ከሂሳቡ ጋር ተያይዞ የሚታየዉ አብዛኞቹ በግዥ እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጨረታ ተለይተዉ አሸናፊ የሆኑ ድርጅቶች ሲሆኑ፣ ክፍያ የሚፈጸመዉ በመጀመሪያ ዕቃዎች ከቀረቡ በኋላ ስለሆነ በቅድሚያ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ አቅርበዉ ንብረቶችን ወደ ዩኒቨርሲቲዉ ገቢ አድርገዉ ሞዴል 19 በማቅረብ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ለማሰባሰብ ድርጅቶቹ በአዲስ አበባ የሚገኙ በመሆናቸዉ ከድርጅቶቹ የደረሰኝ ጥያቄ ቢቀርብም ደረሰኞቹን አሰባስበው ለማምጣት ከቦታ ርቀት እና በቀላሉ ለማሰባሰብ አመቺ ካለመሆኑ አንጻር ረዥም ጊዜ በመዉሰዱ ምክንያት የተከሰተ መሆኑን፣ እና ከግኝቱ ከተጠቀሱት ድርጅቶች በሙሉ ደረሰኞችን በማሰባሰብ ከሂሳብ ሰነዶች ጋር ያያያዙ መሆኑን ጠቅሰው ለወደፊቱ ተመሳሳይ ግዥዎች በሚፈጸሙበት ጊዜ ተመሳሳይ ችግር እንዳያጋጥም ጥንቃቄ በማድረግ እንዲፈጸም እንደሚደረግ ለሥራ አመራሩ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

3.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

- ለሂሳቦቹ በሙሉ ደረሰኞች ተሰብስበው ከሂሳብ ሰነዶች ጋር ተያይዘዋል ቢባልም ለብር 1,538,300.00 እና ለብር 350,542.98 የቀረበ ነገር የለም፡፡

ስለሆነም በግኝቱ በተጠቀሱ ሂሳቦች ላይ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

3.3 በመንግሥት የወጣ ተመን የሌለው ክፍያ፣

3.3.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ተገልጿል፡፡ በዚህ መሠረት ኦዲት ሲደረግ፣

- **በአጼ ቴዎድሮስ ካምፓስ** በቀን 30/06/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 52254 ብር 43,900.00፣
- **በጤና ሳይንስና ህክምና ኮሌጅ**
  - በ28/07/2009 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 689676 ብር 188,000.00፣
  - በ4/13/2008 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 678293 ብር 36,000.00፣ በድምሩ ብር 224,000.00፣
- **በማራኪ ግቢ** በቀን 30/10/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 53889 የክብር ክፍያ /Honorarium/ ብር **8,000.00** እና
- **በመለስ ዜናዊ ግቢ**
  - በ12/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 688431 ብር 6,000.00፣
  - በ23/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 688475 ብር 32,000.00፣
  - በ30/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 688525 ብር 4,000.00፣
  - በ27/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 688495 ብር 24,000.00፣ በድምሩ ብር 66,000.00፣

በጠቅላላ ድምሩ ብር **341,900.00** በመንግሥት የወጣ ተመን ሳይኖር **ከመደበኛ በጀት** ለክብር ክፍያ (Honorarium) መከፈሉ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3.3.2 ስጋት

ማንኛውም ክፍያ ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚከናወን ከሆነ ደንብና መመሪያ እንዲጣስ ሊያደርግና የመንግስትን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

3.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያዎች ከመፈጸማቸዉ በፊት የክፍያዎቹ ህጋዊነትና አግባቢነት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የክፍያዎቹ አስፈላጊነት ከታመነበትም የሚመለከተዉን አካል አስፈቅዶ መሆን ይኖርበታል፡፡

3.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

የሥራ አመራሩ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ለቅድመ ምረቃ እና ድህረ ምረቃ የትምህርት አገልግሎት ለሚከናወኑ ሥራዎች ዩኒቨርሲቲዎች የሚያከናዉኑት ተግባር ከሌሎች ተቋማት የተለየ እና በመማር ማስተማር፣ በምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን በማከናወን የሚፈጸሙ ክፍያዎች በሌሎች የመንግሥት ተቋማት የማይከናወኑ እና ተመሳሳይነት የሌላቸዉ በመሆኑ በፌደራል መንግሥት የክፍያ አፈጻጸም መመሪያዎች የሕግ ማዕቀፍ ዉስጥ ያልተካተቱ በመሆናቸዉ ምክንያት ሥራዎች እንዳይቆሙ ለማድረግ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ በተሰጣቸዉ ስልጣን መሠረት የዉስጥ መመሪዎችን በማዘጋጀት እና በቦርድ በማስጸደቅ ክፍያዎች እየተፈጸሙ የቆዩ ሲሆን፣ በዋና ኦዲተር አስተያየት ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ የክፍያ ተመኖችን መጠን እና የሚከፈሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲፈቀዱ ለፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰዉ ሃብት ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ፐበ01/1892/2009 በቀን 15/10/2009 እንዲሁም ለትምህርት ሚኒስተር በቁጥር ፐበ01/1410/2009 በቀን16/10/2009 በተጻፈ ደብዳቤ ተጠይቆ ክትትል በማድረግ እና ምላሽ እንዲሰጥበት በመጠየቅ በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ክፍያዎች በመቋረጣቸዉ ደግሞ የዩኒቨርሲዉ የመማር ማስተማር ሥራ ጉዳት እየደረሰበት እንደሚገኝ ጠቅሰው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኩል በዩኒቨርሲዎች ወጥ የሆነ አሠራር እንዲዘረጋ አስተያየት እንዲቀርብላቸው በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.3.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ዩኒቨርሲቲው ክፍያዎቹ እንዲፈቀዱለት ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ የተፈቀደ ወጥ የክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ካለ እንዲላክለት ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰዉ ሃብት ልማት ሚኒስቴርን እንዲሁም ትምህርት ሚኒስቴርን በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ አከባቢ በተጻፉ ደብዳቤዎች የጠየቀ ቢሆንም ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት እስከ የከቲት/2010

መጀመሪያ አከባቢ የተሰጠ ምላሽ ስለሌለ አሁንም ቢሆን ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ ክትትሉ ሊቀጥል ይገባል፡፡

3.4 ያለምንም ውድድር በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ፣

3.4.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.1 በአዋጅና በመመሪያ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡
በዚሁ መሰረት የተገዙት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በተመረጡ የግዥ ዘዴዎች እንዲሁም በውድድር መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የዩንቨርሲቲዉን የሥራ ክፍሎች ለመሸለም ከትግስትና ተስፋየ ገጸበረከትና የዕደጥበብ መሸጫ በቀን 26/10/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 696940 የብር 221,353.30 ክሪስታልና ሜዳልያ ግዥ ያለምንም ውድድር የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3.4.2 ስጋት

- ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥም ይችላል፡፡

3.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ

- ዩኒቨርሲቲው ማንኛውንም ግዥ ሲፈፅም በመመሪያው በተገለጹት የግዥ ዘዴዎች መፈጸም ይኖርበታል፡፡
- ከላይ ከመመሪያ ዉጭ የተፈጸመው ግዥም በምን ምክንያት ያለዉድድር እንደተፈጸመ ሊጣራ ይገባል፡፡
- ለወደፊቱም ማንኛውም ግዥ ሲፈጸም ውድድርን መሰረት ያደረገ እንዲሆን የሚመለከተው አካል ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል።

3.4.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

- የሥራ አመራሩ በዚህ ግዥ የተመለከተዉ ዕቃ ክሪስታል እና ሜዳሊ በመሆናቸዉ እና በዚህ ሥራ የተሠማሩ አቅራቢዎች አለመኖራቸዉን በገበያ ጥናት በመረጋገጡ እና በተማሪዎች ምረቃ መቅረብ የነበረበት ስለሆነ እና አስቸኳይ ስለነበረ በተቋሙ ታምኖበት ግዥዉ ቀጥታ የተፈጸመ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

የተማሪዎች ምረቃ በዕቅድ የሚከናወን እና አስቀድሞ የሚታወቅ በመሆኑ በእኛ በኩል የግዥው አስቸኳይነት ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ለወደፊቱ በማሻሽያ ሀሳቡ መሠረት መሥራት ያስፈልጋል፡፡

3.5 <u>የዩኒቨርሲቲው ኢንተርፕራይዝ ሰራተኞችን ደመወዝ በተመለከተ፣</u>

3.5.1 <u>ግኝት፤</u>

የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ማንኛውም የመንግስት ተቋም በተቋሙ ፕሬዚዳንት ጥያቄና በቦርዱ ውሳኔ የገቢ ማስገኛ ድርጅት ሊያቋቁም እንደሚችል እና ድርጅቱ የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ህጉ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት የሚሰራ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በዚህ መሰረት ዩኒቨርሲቲው በህጋዊ መንገድ ያቋቋማቸው የጃንተከል ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ እና የብሩህ ሆቴልና መስተንግዶ ኢንተርፕራይዝ የራሳቸውን ወጪ በራሳቸው ገቢ እንዲሸፍኑ ማድረግ ሲገባ፣

- በዓጼ ቴዎድሮስ ግቢ ለብሩህ ሆቴልና መስተንግዶ ኢንተርፕራይዝ ሠራተኞች ደመወዝ ብር 501,073.00 እና
- በማራኪ ግቢ ለጃንተከል ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ ሰራተኞች ደመወዝ ብር 211,303.34፣

በድምሩ ብር 712,376.34 በበጀት ዓመቱ ከመደበኛ በጀት ለደመወዝ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዞቹ የራሳቸው የሆነ ልዩ ልዩ የስራ መመሪያዎች እና በዩኒቨርስቲው ስራ አመራር ቦርድ የጸደቀ የገቢ ማስገኛ የሌላቸው መሆኑ ፤

(ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 2 ተያይዟል፡፡)

3.5.2 <u>ስጋት</u>

- በስራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ደንቦችና መመሪያዎች በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ የማይሆኑ ከሆነ ለብልሹ አሰራር በር ከፋች ይሆናሉ፡፡
- ኢንተርፕራይዞቹ ወጪያቸውን በራሳቸውን ገቢ መሸፈን ሲገባ ለዩኒቨርሲቲው

ከተመደበ መደበኛ በጀት የደመወዝ ክፍያ መክፈል በጀቱ ለታለመለት አላማ ውሏል ለማለት አያስችልም፡፡

3.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ

- የገቢ ማማንጫ ድርጅቶቹ የራሳቸው ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ሆነው እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ህጉ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት የሚሰሩ እስከሆነ ድረስ የራሳቸው የሆነ ልዩ ልዩ የስራ መመሪያዎች ቦርዱ እንዲያጸድቃቸው በማድረግ በስራ ላይ እንዲያውሉ ማደረግ አለበት፡፡
- ኢንተርፕራይዞቹ የራሳቸውን ወጪ በራሳቸው ገቢ እንዲሸፍኑ ተብለው እስከተቋቋሙ ድረስ ለኢንተርፕራይዞች ከመደበኛ በጀት የሚከፈሉ ማናቸውም ክፍያዎች መቆም ይኖርባቸዋል፡፡

3.5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

የሥራ አመራሩ፡-

- ከአሁን በፊት ኢንተርፕራይዞችን ራሳቸዉን እስከሚችሉ ድረስ በሰዉ ሃይል እና በቁሳቁስ እንዲደገፉ በማድረግ፣ በተለይም የኢንተርፕራይዞች ሠራተኞችን የሥራ መደብ በፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰዉ ሃብት ልማት ሚኒስቴር በማስፈቀድ ሲሰራ የቆየ መሆኑን፤ የኢንተርፕራይዞችን የሥራ መመሪያዎች ለማስጸደቅ ለቦርድ አጀንዳ ተቀርጾ የቀረበ ሲሆን፣ የተለያዩ መመሪዎችን እና የገቢ ማስገኛዎች በማስጸደቅ ወደ ሥራ እንዲገባ እንደሚደረግ፣ እና
- በጃን ተከል ማተሚያ ድርጅት በ 2009 የበጀት ዓመት የተከፈለዉን የገንዘብ መጠን ብር 237,493.81 ለብሩህ ሆቴል እና መስተንግዶ የተከፈለዉን ደመወዝ ብር 501,073.00 በተሰብሳቢ እንዲመዘገብ የተደረገ ሲሆን፣ በ2010 የበጀት ዓመት ከኢንተርፕራይዞች ተሰብስቦ ገቢ እንደሚደረግ ገልጸው፤

ለወደፊትም ኢንተርፕራይዞች አትራፊ መሆን አለመሆናቸዉን ለመቆጣጠር እና ዉጤታማነታቸዉን ለማሻሻል እንዲቻል የደመወዝ እና ተዛማጅ ወጭዎች በየኢንተርፕራይዞች እንዲሸፈኑ እንደሚደረግ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.5.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ገንዘቡ ክትትል ተደርጎበት ሂሳቡ ከኢንተርፕራዞቹ ላይ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

3.6 በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች፣

3.6.1 ግኝት፣

ሰኔ/2002 ባወጣው የፌዴራል መንግስት የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 3 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የተለያዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ከአቀራቢዎች/ከስራ ተቋራጮች/ ጋር የተደረገውን የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ እንደሚኖርባቸው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረው የዩኒቨርሲቲው የግንባታ የውል አፈጻጸም ሲታይ የሥራ ተቋራጮች 4 ግንባታዎችን በውላቸው መሰረት ማጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ21 እስከ 187 ቀናት ያዘገዩ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከላይ ከተጠቀሱ ግንባታዎች ውስጥ ሎት-19 ፐብሊክ ሄልዝ ግንባታ የሚገነባው ክራፍት ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ ሥራ ተቋራጭ ግንባታውን እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ለ187 ቀናት ከማዘግየቱ በተጨማሪ 181 ቀናት የፀደቀ የውል ማራዘሚያ ጊዜ ተሰጥቶት እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

(ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 3 ተመልክቷል፡፡)

3.6.2 ሥጋት፣

- የግንባታው የስራ ሂደት በታቀደለት ጊዜ አለመጠናቀቁ ከግንባታው ጋር ተያይዞ አገልግሎት የሚያገኘው አካል ተጠቃሚ እንዳይሆን ከማድረጉም ባሻገር የግንባታ ዕቃዎች ከዋጋ መጨመር አንፃር መንግስትን ላልተፈለገ ወጪ ሊዳርገው ይችላል፡፡
- ግንባታዎች በውላቸው መሰረት ባለማለቃቸው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡

3.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኮንትራክተሮች ግንባታዎቹን በስምምነቱ መሰረት ጨርሰው እንዲያስረክቡ ክትትል ማድረግና በታቀደለት የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቅ የሚያደርጉትን ቁልፍ ችግሮች ለይቶ በማውጣት ከበላይ የማኔጅመንት ሀላፊዎች ጋር በመነጋገር መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግና በኮንትራክተሩ ምክንያት በሚጓተቱ የግንባታ ስራዎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

3.6.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ፣ የተሰጡትን መወሰድ ያለበቸው የማሻሻያ እርምጃዎች ተቀብለው የተሰጣቸውን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ከዚህ ቀደም ሌሎች ግንባታዎች እንዲጠናቀቁ እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ካደረጉባቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተሻለና በበለጠ የሚሠሩ መሆኑን ገልጸው፣

- ግንባታዎች በታቀደላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ከዚህ ቀደም ከነበረው ክትትል በበለጠ አጠናክረው መቀጠልና በታቀደለት የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቅ የሚያደርጉትን በሥራ ተቋራጮች በኩል የሚከሰቱትን ቁልፍ ችግሮችን (ለምሳሌ አጠቃላይ የማስተዳደርና የመስራት አቅም ዘመናዊነት ከማሳደግ አንጻር አጥጋቢ ሥራ አለመስራት፣ ለሚሰሩት ስራ በቂ ትኩረት አለማድረግና ቸልተኝነት፣ ለተሰራ ስራ የተከፈላቸውን ክፍያ በአግባቡ ለፕሮጀክቱ አለመጠቀም፣ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ድርጅታዊም ሆነ ሃገራዊ ችግሮች ለይተው በአፈጻጸማቸው ላይ ተጽእኖ እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ችግሮቹ እንዳይከሰት ተገቢውን ስራ ያለመስራት እና መከሰታቸው አይቀሬ ለሆኑ ችግሮች የሚገባቸውን ቅድመ ጥንቃቄ አለማድረግ፣ የሚያጋጥማቸውን ድርጅታዊም ሆነ ሃገራዊ ችግሮች ለመቅረፍ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ፣ በስራ ተቋራጮች ሊፈቱ የማይችሉ ችግሮችን ለይቶ ግንባታውን ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ አማራጭ መንገዶችን ያለመንደፍና ያለመተግበር እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ያላቸውን አጠቃላይ ተጽእኖ) ለይተው በማውጣት እንደየደረጃው እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ የሥራ ተቋራጮች ላይ እርማጃ በመውሰድ፣ ድጋፍ እና ክትትል የሚያስፈልጋቸውን አሁን ከሚያደርጉት በላይ አጠናክረው በመቀጠል፣ የዩኒቨርሲቲውና የአማካሪ ድርጅት ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም የሥራ ተቋራጭ ድርጅት ባለቤቶች በተገኙበት የሚደረገውን የጋር የቁጥጥር እና መፍትሄዎችን የማስቀመጥ መድረክ አጠናክሮ በመቀጠል ችግሮች እልባት እንዲያገኙ፣ መንግስት በዘላቂነት ተጠቃሚ የሚሆንበትን አማራጭ ለመጠቀም ያለሰለሰ ጥረት እንደሚያደርጉ፣
- ግንባታዎች በታቀደላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ከዚህ ቀደም ከነበረው ክትትል በበለጠ አጠናክረው መቀጠልና በታቀደለት የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቅ የሚያደርጉትን በዩኒቨርሲቲው እና በመንግስት በኩል የሚከሰቱትን ቁልፍ ችግሮችን

(ለምሳሌ የምህንድስና አገልግሎት ዳይሬክቶሬትን አቅም ከማሳደግ፣ ለተሰራ ስራ የሚከፈል ክፍያ ከመዘግየት፣ የውጭ ምንዛሬ በተገቢው ጊዜ ከማግኘት /Letter of Credit/፣ ምንዛሬ ከመጨመርና ከሚፈጥረው ተጽእኖ፣ የማጠቃለያ ግብዓቶችን /Finishing Materials/ በቀላሉ በሃገር ውስጥ ገበያ ላይ ካለማግኘት፣ የሥራ ተቋራጮችን አጠቃላይ የማስተዳደርና የመስራት አቅም ዘመናዊነት ከመፈተሽና ከማሳደግ አንጻር እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ያላቸውን አጠቃላይ ተጽእኖ) ለይተው በማውጣት እንደየደረጃው ከዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራር፣ የሥራ አመራር ቦርድ እና ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በመነጋገርና በጋራ በመስራት የሚቻለውን ያክል መፍትሄ እንዲያገኙ ለማድረግ እንደሚሰሩ እና

- ከዚያ ባለፈም ችግሮቹ በዘላቂነት የማይፈቱ ከሆነም ሊተገበሩ የሚችሉ አማራጭ የችግር መፍቻ ዘዴዎችን በመጠቀም ችግሩ እልባት እንዲያገኝ ያለሰለሰ ጥረት እንደሚያደርጉ፣
- በመጨረሻም በአንድ ግንባታ መጓተት ላይ በሥራ ተቋራጩ ችግር ምክንያት የተከሰተውን እና ከሥራ ተቋራጩ ግዴታ ውጪ በሆነ ምክንያት የሚከሰቱ የግንባታ መጓተትና ደካማ አፈጻጸሞች እርስበርስ የተደራረቡ በመሆኑና ለመለየት አስቸጋሪ እየሆነ በመምጣቱ ብቁ ያልሆኑና ችግር ያለባቸውን የሥራ ተቋራጮች እና መልካም አፈጻጸም ያላቸውን የሥራ ተቋራጮች ለመለየት አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱን ገልታ ይህ ጉዳይ በሃገር ደረጃ በግንባታ ዘርፉ ላይ ተጽእኖ እንዳይፈጥር የጋራ ርብርብ እንደሚያስፈልግ በምላሻቸው ገልጸዋል።

4. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

4.1 <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

4.1.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ ”ለ” የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ07 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና ንዑስ አንቀጽ “መ” ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡

በዚህ መሠረት የዩኒቨርሲቲው ተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣ በዩኒቨርሲቲው የሰኔ 30/2009 ዓ.ም የሂሳብ ሪፖርት ላይ በአጠቃላይ ድምር ብር **47,163,331.14** ተሰብሳቢ ሂሣብ በውዝፍ የተገኘ ሲሆን ይህም፣

- ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያዎች /suspense 4201/ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ተመላሽ መደረግ /መወራረድ/ ሲገባ ከ1995 እስከ 2009 ዓ.ም በተለያዩ ግለሰቦች እጅ የቆየ ብር 2,046,074.32 መሆኑ፣
- Advance to staff /4203/ ገንዘቡ ወጪ የሆነበት ከሀምሌ 01/2000 ዓ.ም ጀመሮ እስከ 30/10/2009 ድረስ ብር 224,759.89 የቆየ መሆኑ፣
- በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያ /other Advances to BI 4209/ የተያዘና ከ1 ዓመት እስከ 9 ዓመት የቆየ ብር 16,461.99 መሆኑ፣
- ከግዢ ከተመራማሪዎችና ከሌሎች ቅድሚያ ክፍያ /Purchase Advance 4211/ የተያዘና በመመሪያው መሰረት በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ሳይወራረድ ቀርቶ በግዢ ሰራተኞች እጅ የሚገኝ ከአንድ ዓመት እስከ ሰባት ዓመት የቆየ ብር 6,635,525.41 መሆኑ፣
- ለዕቃ አቅራቢዎች በሚፈጸም የቅድሚያ ክፍያ/Advance to suppliers 4253/ የተያዘና በመመሪያው መሰረት ከ30 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መወራረድ ሲገባ ሳይወራረድ የቆየ ብር 1,222,259.99 መሆኑ፣ እና
- በሂሳብ መደብ 4273 ገንዘቡ ወጪ የሆነበት ከሀምሌ 01/2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2009 ድረስ የቆየ ብር 11,445,831.07 መሆኑ፣

በድምሩ ብር **21,590,912.67** ሳይሰበሰብ ከ1 ዓመት እስከ 13 ዓመት የቆየ መሆኑ፣

- በ4251 የሂሳብ መደብ (ለሥራ ተቋራጮች ቅድመ ክፍያ) ተሰጥቶ እያለ በበጀት ዓመቱ (2009 በጀት ዓመት):-
  - ለልደታ አርቲዛን በ18/10/07 የተከፈለ ብር 7,381.21፣
  - ለመንገሻ መንክር በ01/02/06 የተከፈለ ብር 400,536.93፣
  - ለአስማማው አለነ ብር 5,182,743.99፣
  - ለኑርነት ኃ/የተ/የ/ማህበር በ08/10/04 የተከፈለ ብር 1,020,376.83፣
  - ለሲምፖል ቴክኖሎጅ በ10/07/07 የተከፈለ ብር 477,153.31፣
  - ለልደታ አርቲዛን በ12/02/07 የተከፈለ ብር 22,905.20፣

- ለስንታየሁ አያለው በ12/02/08 የተከፈለ ብር 868,500.00፣
- ለፐሮኔት ኢንተርናሽናል ሰርቪስ ኃ/የተ/የ/ማህበር በ18/05/08 የተከፈለ ብር 233,710.30፣
- ለሌዘር ኮምፒውተር ትሬዲንግ በ03/06/02 የተከፈለ ብር 212,895.23፤
- ለኤም ኤፍ ትሬዲንግ በ10/06/2003 የተከፈለ ብር 199,611.29፣
- ለአኪር ኮንስትራክሽን በ14/04/03 የተከፈለ ብር 14,545,365.82፣
- ለብሩክ ገዛሀኝ በ01/11/2000 የተከፈለ ብር 2,401,238.36፣

በድምሩ ብር **25,572,418.47** መሆኑ፤

ታውቋል፡

4.1.2 ስጋት፣

- በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለው የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- በተጨማሪ ሂሳቡን ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊያደርስ እና ባክኖ እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል፡፡

4.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

- ያልተወራረደው ተሰብሳቢ ሂሳብ በሚመለከታቸው አካላት እንዲወራረድ ሆኖ ለወደፊቱ የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

በሰኔ 30/2009 ዓ.ም የሂሳብ ሪፖርት ላይ ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያዎች: -

- **በ4201 የሚታየዉ ሚዛን** ብር 2,046,074.32 ላይ ብር 1,957,491.28 ለረዥም ጊዜ የቆየ ተሰብሳቢ ከመሆኑም በላይ ከዚህ ዉስጥ ብር 1,586,527.78 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚፈለግ እንደሆነ የሂሳብ ሚዛኑ የሚያሳይ ሲሆን፣ ቀሪዉ ብር 370,963.50 ከልዩ ልዩ ግለሰቦች የሚፈለግ በመሆኑ ምክንያት መረጃዎችን ለማጣራት ጥረት ተደርጎ ሰነዶችን ለማስወገድ ታቅዶ ለጎንደር ከተማ አስተዳደር ደብዳቤ በድጋሚ ተጽፎ በመጣራት ላይ ያለ ስለሆነ እንደተጠናቀቀ የሚከናወን መሆኑን፤

ሌሎች ግን በየጊዜዉ ክትትል እየተደረገ እየተሰበሰበ የሚገኝ እና የዘመኑንም የሚያካትት መሆኑን፣ (**ለከተማ አስተዳደሩ የቀረበ ጥያቄ 1 ገጽ እና የተቀጽላ ሌጀሮች ኮፒ 2 ገጽ፣ በድምሩ 3 ገጽ ቀርቧል**)

- **በ4203 እና በ4209** የሚታዩ ሚዛኖች ቀደም ሲል ከላይ በ4201 እንደተገለጸዉ ሁሉ ለረዥ ጊዜ የቆዩ ተሰብሳቢዎች በመሆናቸዉ በከተማ አስተዳደሩ የማጣራት ሥራ እየተሠራ መሆኑን እና በሚገኘዉ መረጃ መሠረት ተጨማሪ ርምጃዎችን ለመዉሰድ ጥረት የሚደረግ መሆኑን፣ የየዘመኑ ተሰብሳቢ ግን በወቅቱ የተወራረደ መሆኑን፣
- በ4211 በተሰብሳቢ የሚገኘዉ የዕቃ ግዥዎች ብቻ ሳይሆን ከተመራማሪዎች እና የሌሎችንም ቅድሚያ ክፍያ የሚያካትት ሲሆን፣ መሰብሰብ የሚገባቸዉን ከበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቀጥሎ ባለዉ ወር በሐምሌ ወር 2009 የተሰበሰቡ ሲሆን፣ ቀጣይም ክትትል በማድረግ የተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲሰበሰብ እንደሚደረግ፣
- በ4251 በተሰብሳቢ የሚታዩ ተብለዉ ከተገለጹት ድርጅቶች ውስጥ፡-
    1. ለዮሀንስ አባይ ብር 7,381.21 የነበረበት ቢሆንም ዉለታዉ ያልተጠናቀቀ ስለሆነ በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ድርጅት በመሆኑ እስከ 2010 የሥራ እንቅስቃሴ ያለዉ እና የነበረበት ዕዳ ሙሉ በሙሉ የከፈለ መሆኑን እና በአሁኑ ሰዓት ምንም ዓይት ዕዳ የሌለበት መሆኑን፤
    2. ለመንገሻ መንክር ብር 400,536.93፡- በሥራ ላይ የሚገኝ እና በ2010 የበጀት ዓመት እንቅስቃሴ ያለዉ መሆኑን፤
    3. ለአስማማው አለን ብር 5,182,743.99፡- በሥራ ላይ የሚገኝ ዉለታዉ ያልተጠናቀቀ እና በ2010 የበጀት ዓመት በሌጀሩ የሚታየዉ ሚዛን ብር 1,078,981.75 መሆኑን፤
    4. ለአኪር ኮንስትራክሽን ብር 14,545,365.82፣ ሥራዉን በማጓተቱ ምክንያት ዉሉ እንዲቋረጥ የተደረገ እና በክስ ሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣
    5. ለሲምፖል ቴክኖሎጅ ብር 477,153.31 አሁንም ዉለታዉ ያልተጠናቀቀ እና በሥራ ላይ ያለ ድርጅት መሆኑን እየገለጽን ከዚያ በኋላ ተጨማሪ የሥራ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኝ መሆኑን፤
    6. ለኒዉሮኔት ኃ/የተ/የ/ማህበር ብር 1,020,376.83፤ ለልደታ አርቲዛን ብር 22,905.20፣ ለስንታየሁ አያሌው ብር 868,500.00፤ ለፕሮኔት ኢንተርናሽናል

ሰርቪስ ኃ/የተ/የ/ማህበር ብር 233,710.30፣ ለሌዘር ኮምፑተር ትሬዲንግ ብር 212,895.23፣ ለኤም ኤፍ ትሬዲንግ ብር 199,611.29፣ ለብሩክ ገዛሀኝ ብር 2,401,238.36 ምክንያታቸዉን በማጣራት ምላሽ የሚያቀርቡ እና እንደአስፈላጊነቱ ተከታታይ ማስተካከያዎችን የሚወስዱ መሆኑን፣

- በ4253 - የሚፈለግባቸዉ አቅራቢዎች መረጃ ተጣርቶ አቅራቢዎች ገቢ እንዲያደርጉ ማስረጃዎችን ማደራጀታቸውን እና በህግ ለመጠየቅ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን፣
- በ4273 ለተለያዩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የተፈጸመ ክፍያ ተሰብሳቢ ዉስጥ፣
  - በተሰብሳቢ የሚታዩት ሂሳቦች ከባለ ዕዳዎች ማስረጃዎችን በመያዝ እንዲሰበሰቡ እነረደሚደረግ፣ እና
  - ሌሎች ተሰብሳቢዎች ደግሞ አንዳንዶች የመንግሥት መ/ቤቶች ሆነዉ አገልግሎት ቢሰጡም የገቢ ደረሰኝ አልቀረበም በሚል በወጭ ሳይመዘገቡ የተገኙ ክፍያዎች መሆናቸዉን፣ በግለሰቦች የሚታዩ ተሰብሳቢዎችን ደግሞ በማጣራት የሚሰበሰቡ መሆናቸዉን ገልጸዉ፣

በአጠቃላይ በተሰብሳቢ የሚታዩ ሚዛኖችን ለማሰባሰብ በየበጀት ዓመቱ ጥብቅ አሠራር ተዘርግቶ እየተተገበረ የሚገኝ ሲሆን ረዥም ጊዜ የቆዩ ተሰብሳቢዎችን ግለሰቦችን እና ድርጅቶችን በደብዳቤ ከመጠየቅ በተጨማሪ ወደ ህግ አገልግሎት የሚላኩትን በመላክ በህግ አግባብ ለመጠየቅ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን እና የየዘመኑ ተሰብሳቢ ደግሞ እንዳይከማች ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ በወቅቱ እንዲሰበሰብ መደረጉን ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4.2 ተቀጽላ ሌጀር የሌለው ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

4.2.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ

8 ንዑስ አንቀጽ 4/መ እና ረ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ፣ ንዑስ አንቀጽ 4/ረ ደግሞ ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተከፍቶለት ክትትል መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

በዚሁ መሰረት **በዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል** በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታየው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፡ የሆስፒታሉ የሰኔ 30/2009 ዓ.ም የተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገቢያ (አይ ቤክስ) ላይ የሚታየው በሂሳብ መደብ 4201 በልዩ ልዩ የተሰብሳቢ ሂሳቦች ብር 8,560.86 እና በሂሳብ መደብ 4202 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ብር 29,947.15፣ በድምሩ ብር **38,508.01** ከማን እንደሚሰበሰብ ለማወቅ ይቻል ዘንድ በእያንዳንዱ ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተለት እና ክትትል የማይደረግ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

4.2.2 ሥጋት

የሆስፒታሉ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶለት ክትትል የማይደረግ ከሆነ እዳዉ ከማን እንደሚሰበሰብ ላይታወቅ ይችላል፡፡

4.2.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ተቀጽላ ሌጀር ላልተከፈተለት የሆስፒታሉ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከማን እንደሚሰበሰብ የሚገልጽ ተቀጽላ ሌጀር ሊከፈትለትና ክትትል ለደረግበት ይገባል፡፡

4.2.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፤**

የሥራ አመራሩ በሆስፒታል ግቢ የተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተላቸዉ ተሰብሳቢ ሂሳቦች የተቀጽላ ሌጀር እንዲከፈትላቸዉ መደረጉን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

5. ተከፋይ ሂሳብ

5.1 በወቅቱ ያልተወራረደ ተከፋይ ሂሳብ፤

5.1.1 ግኝት፤

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሀ ማንኛውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበትና ንዑስ አንቀጽ 5/መ ደግሞ ለእያንዳንዱ ተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተከፍቶለት ክትትል መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

በዚሁ መሰረት በዩኒቨርሲቲው በተከፋይ ሂሳብ የሚታየው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም መከፈል ሲገባ ያልተከፈለ በድምሩ ብር 34,323,631.25 ከ1 ወር እስከ 10 ዓመት የቆየ በተከፋይነት የሚታይ ሂሳብ የነበረ ሲሆን ይህም፣

- በሂሳብ መደብ 5002 በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች /sundry creditors/ ብር 33,509,097.04 የተያዘ መሆኑ፣
- በደመወዝ ተከፋይ ሂሳቦች /salary Payable 5004 /የተያዘ ለሰራተኞች የሚከፈል ደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ሲሆን ክፍያው ለሰራተኞች ተከፍሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ መወራረድ የሚገባቸው ሂሳቦች ቢሆንም ለባለመብቱ ሳይከፈልና ሳይወራረድ የተገኘ ብር 221,851.15 መሆኑ፣
- በልዩልዩ የደመወዝ ተቀናሽ /other Payroll deduction 5005/ የተያዘ ከሰራተኞች ለተለያዩ አገልግሎት የተሰበሰበና ለባለመብቱ ተከፍሎ መወራራድ ሲኖርበት ሳይወራረድ የተገኘ ብር 7,332.32 መሆኑ፣
- በመያዣ /Hospital Deposite 5053/ የተያዘ በዩኒቨርቲው ሆስፒታል ተመዝግቦ የሚገኝና መወራረድ ሲገባ ሳይወራረድ የተገኘ ብር 582,260.74 መሆኑ፣
- በተለያዩ መያዣዎች /Other Deposit 5054/ ተመዝግቦ የሚገኝና መወራረድ ሲገባ ሳይወራረድ የተገኘ ብር 3,090.00 መሆኑ፣

መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

5.1.2 <u>ስጋት</u>

የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ካልተወራረደ ወይም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደበት የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

5.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ተከፋይ ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

5.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

- ➢ በ5002 በተከፋይ የሚታየዉ ገንዘብ በማጣራት ለባመብቶች በመከፈል ላይ የሚገኝ መሆኑን፣
- ➢ በ5004 የተያዘዉ ተከፋይ ላይ መከፈል የሚገባዉን ገንዘብ ለመክፈል ጥረት የተደረገ ሲሆን ለወደፊቱም ቀሪ ተከፋዮችን ሙሉ በሙሉ እንደሚከፍሉ፣

- በ5005 የተያዘዉን ልዩ ልዩ ተከፋዮች በማጣራት ለባለመብቶች ክፍያዎችን እንደሚፈጽሙ፣
- በ5053 የሆስፒታል ማስያዣን በተመለከተ በየጊዜዉ ማጣራት በማድረግ ለባለ ጥቅሞቹ የሚከፈል ቢሆንም አንዳንድ ታካሚዎች በተለያየ ምክንያት ሂሳባቸዉ ሳይዘጉ የሚጠፉ በመሆናቸዉ የተከሰተ ሲሆን፣ አሁንም በማጣራት የሚታየዉን ተከፋይ የሚከፍሉ መሆኑን፣
- በ5054 ልዩ ልዩ ማስያዣዎች የሚታየዉን ብር 3,090.00 በማጣራት ለባመብቶች የሚከፈል መሆኑን፣

በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

5.2 ተቀጽላ ሌጀር የሌለው ተከፋይ ሂሳብ፣

5.2.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ

8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሀ ማንኛውም ወደ ፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት፣ ንዑስ አንቀጽ 5/መ ደግሞ ለእያንዳንዱ ተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተከፍቶለት ክትትል መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

በዚሁ መሰረት በየካምፓሱ በተከፋይ ሂሳብ የተያዘው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣

- **በመለስ ዜናዊ ካምፓስ** ሰኔ 30/2009 ዓ.ም በተከፋይ ሂሳብ መመዝገቢያ (አይ ቤክስ) ላይ በሂሳብ መደብ 5002 በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች ለተያዘ ብር 692,724.91፣ እና
- **በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ተከፋይ ሂሳብ መመዝገቢያ (አይ ቤክስ) ላይ በሂሳብ መደብ 5002 በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች ለተያዘ ብር 16,711.22፣

በድምሩ **709,436.13** ብር ለማን እንደሚከፈል ለማወቅ የሚያስችል በያንዳንዱ ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተለት መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

5.2.2 ሥጋት

የኮሌጆቹ ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶላቸው ክትትል የማይደረግ ከሆነ እዳዉ ለማን እንደሚከፈል እንሚከፈል ላይታወቅ ይችላል፡፡

5.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ተቀጽላ ሌጀር ላልተከፈተላቸው የኮሌጆቹ ተከፋይ ሂሳብ ለማን እንደሚከፈል የሚገልጽ ተቀጽላ ሌጀር ሊከፈትላቸው ይገባል፡፡

5.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ በምላሻቸው፣

- በሕጤሳኮ ግቢ እና በመለስ ዜናዊ ግቢ የተቀጽላ ሌጀር በመክፈት ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ ተቀጽላ ሌጀር ለመክፈት ያልተቻለበት ምክንያት፡-
  - በባንክ ለሚከፈል ደመወዝ እና ተዛማጅ ክፍያዎች ባንኩ ወደ ዩኒቨርሲቲዉ የባንክ ሂሳብ ሲመልስ ለማ እንዳልከፈለ ባለመግለጹ ምክንያት የማን እንደሆነ በማጣራት ተቀጽላ ሌጀር ለመክፈት መረጃ ከባንኩ የተጠየቀ መሆኑን፣
  - ለአንድ ዕቃ ግዥ ሠራተኛ ለግዥ ሠራተኛ ቅድሚያ ክፍያ የተሰጠ ሂሳቡ ሲወራረድ በብልጫ ገቢ ያደረገው ብር 7,835.85 በማጣራት ላይ ይገኛል፣
  - ለወ/ሮ የሻለም ለገሰ የሚከፈል ብር 199.96 (አንድ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም) በሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም የተከፈለ፤
  - የሌሎች የተቀጽላ ሌጀር እንዲከፈት የተደረገ ሲሆን ማስረጃዉ ተያይዟል፣

ብለዋል፡፡

5.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የሥራ አመራሩ በግኝቱና የማሻሸያ ሀሳቡ ላይ የሰጠው ምላሽ ብዙም የጠራ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ባጠቃላይ በግኙቱ ላይ በማሻሸያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

6. በጀት፣

6.1.1 ግኝት

በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሣብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡

በዚህ መሠረት የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 እና በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ከሐምሌ/2008 እስከ ሰኔ 30/2009 የዩኒቨርሲቲው የተስተካከለ በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር፣

- ከመደበኛ በጀት ብር 16,877,890.26 ከየሂሳብ መደቡ ከ10% በላይ ሥራ ላይ አለመዋሉ፣
- ከመደበኛ በጀት ብር 8,276,364.62 እና ከካፒታል በጀት ብር 337,902.98፣ በድምሩ ብር 8,614,267.60 ከተፈቀደው በጀት በላይ ሥራ ላይ መዋሉ፣

ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 3 ተያይዟል፡፡

6.1.2 ስጋት፤

- የተፈቀደን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ አለማዋል በበጀት ዓመቱ በዕቅድ የተያዙ ስራዎች እንዳይከናወኑ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ በሌሎች መ/ቤቶች ሊሰራበት የሚችለው በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡
- የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል እና ከተፈቀደዉ በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

የሥራ አመራሩ፣

- **በመደበኛ በጀት ከበጀት በላይ ሥራ ላይ የዋሉት የወጭ ሂሳብ መደቦች፡-**
  - የኮንትራት ሠራተኞች ደመወዝ፣ የቀን ሠራተኞ ምንዳ እና ለሠራተኞች የሚከፈሉ ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች በተጨማሪ በጀት እና በበጀት ዝዉዉር ለማካካስ ጥረት ቢደረግም ሊሳካ ስላልቻለ እና የግዴታ ወጭዎች በመሆናቸዉ ሥራ እንዳይቆም በብልጫ የተከፈለ መሆኑን፣

- ለደንብ ልብስ እና ለምግብ የወጡት ወጭዎችም በተመሳሳይ ቀደም ሲል የታቀደዉ ፍላጎት የግዴታ ወጭ በመሆኑ ምክንያት የበጀት ዝዉዉር ለማድረግ ጥረት ተደርጎ በበጀት ማተስካከያ የተጨመረዉ በጀት በወቅቱ ከነበረዉ የዋጋ መጨመር ጋር ሊጣጣም ስላልቻለ እና የግዴታ ወጭ በመሆኑ የተፈጸመ ክፍያ መሆኑን፣
- 6251፣ 6256፣ 6271 ለተለያዩ የመማር ማስተማር እና የምርምር ሥራዎችን ለማከናወን የግዴታ ወጭዎች ሲሆኑ፣ በተለያዩ ምክንያቶች የዋጋ ጭማሪ እና መጀመሪያ ከታቀደዉ ጋር ልዩነት ያመጣ ቢሆንም ሥራዉ መቆም የማይችል በመሆኑ የተፈጸመ ክፍያ መሆኑን፣
- በሌሎችም የወጭ ሂሳብ መደቦች በታቀደዉ እና በተፈጸመዉ መካከል ልዩነት በመኖሩ ምክንያት ከበጀት በላይ ሥራ ላይ መዋሉን፣

በካፒታል በጀት ከበጀት በላይ ሥራ ላይ የዋሉት የወጭ ሂሳብ መደቦች፡-

- በካፒታል በጀት የመሥክ ሥራዎች አስፈላጊ በመሆናቸዉ ምክንያት ሥራዎች ሊቆሙ የማይችሉ እና ከዩኒቨርሲቲዉ መደበኛ ሥራዎች ጋር የተያያዙ በመሆናቸዉ ምክንያት የዉሎ አበል ክፍያ በታቀደዉ እና በአፈጻጸም ልዩነት ምክንያት ከበጀት በላይ ሥራ ላይ መዋሉን፣

በመደበኛ በጀት ከበጀት በታች ሥራ ላይ የዋሉት ፡-

- የዕቃ እና አገልግሎት ግዥዎች ጨረታ ወጥቶ እንዲሁም በማዕቀፍ ግዥም ከፌደራል መንግሥት የግዥ እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ከተገዛባቸዉ አቅራቢዎች የቀረቡ ዕቃዎች የሚፈለገዉ ሞዴል፣ የጥራት ደረጃ እና ብዛት ሳይገኝ ሲቀር በጀቱ ሥራ ላይ ባለመዋሉ ምክንያት የተከሰተ መሆኑን፣
- የአገልግሎት ክፍያዎች እንደ ማስታወቂያ፣ ኤሌክትሪክ፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት፣ የዉሃ እና የፖስታ አገልግሎቶች ቢሎች እና ደረሰኞች በወቅቱ ያልቀረቡ በመሆናቸዉ ምክንያት በወጭ በማጽደቅ ክፍያዎችን ለመፈጸም ስላልተቻለ መሆኑን ጠቅሰው፣

በአጠቃላይ የበጀት አጠቃቀምን ለማሻሻል ዩኒቨርሲቲዉ የራሱን የዉስጥ አሠራር ዘርግቶ ሥራ ላይ ያዋለ ሲሆን፣ የበጀት ቁጥጥር ሥርዓትን በማሻሻል የበጀት አጠቃቀምን በዕቅድ በመመራቱ የበጀት አጠቃቀሙ በየበጀት ዓመቱ እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን እና፣

ዩኒቨርሲቲዉ የበጀት አጠቃቀምን የበለጠ ለማሻሻል እና በታቀደዉ መሠረት ብቻ ሥራ ላይ እንዲዉል ለማድረግ አበክሮ የሚሠራ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

7. ንብረት፣

7.1 አላቂና ቋሚ ዕቃዎች፣

7.1.1 ግኝት፣

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በእቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ፡-

- በንብረት መጠበቂያ መጋዘኖች ውስጥ የሚገኙት የተወሰኑ እቃዎች በዓይነት፣ በባህሪይና በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በሥርዓት ያልተቀመጡ መሆኑ፣
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ በዕርዳታ ከCentre for International Unique in Ethiopia የተገኙ የህክምና ዕቃዎች በዩኒቨርሰቲው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) የተዘጋጀላቸው ቢሆንም ዋጋቸው ያልተጠቀሰ መሆኑ (ለምሳሌ፡- ሞ/19 ቁጥር 814351-814400)፣
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጡ አዳዲስ ንብረቶች፣ ለምሳሌ፡- 14 የኮንፈረንስ ቴብል፣ 4 የገንዘብ ካዝናዎች፣ 7 ሲፓፕ የህክምና ማሽን፣ 81 ለብዙ ጊዜ የቆዩ የተለያዩ ሰሌዳዎች፣ 16 ኢንፌንታ ራዲያተርና እንኩቤተር፣ 86 ዌይት ስኬል (ሚዛን)፣ የመሪ ዘይት፣ 528 የቧንባ ዕቃዎች መኖራቸው፣
- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የፕሪንተር እና የፎቶ ኮፒ ቀለሞች፣ ላርጎ ሳሙና እና የተለያዩ የደምብ ልብሶች ክፍሉን አጣብበው መቀመጣቸው፣
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ አራት ምን እንደያዙ ያልታወቀ ሲሊንደሮች አሲድ መያዙን አለመያዙን ያልታወቃ መሆኑንና ከንብረት ጋር ስቶር ዉስጥ ለዓመታት ተቀምጦ መገኘቱ፤
- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ አገልግሎት አይሰጡም ተብሎ የተመለሱ እንደ ዩፒኤስ ብዛት 202፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን ብዛት 30፣ እስቴትስኮፕ ብዛት 165፣ የብረት ወንበር ብዛት 7፣ የተለያዩ ሞባይሎች ብዛት 09፣ ቶሽባ ላፕ ቶፕ ብዛት 107፣ ኤችፒ ላፕ ቶፕ ብዛት 28፣ ታይፕራይተር ብዛት 29፣ ዴል ኮምፒዩተር ሲስተም ብዛት 128፣ ኤችፒ ሲስተም ብዛት 40፣ ኤችፒ ሞኒተር ሲስተም ብዛት 90፣ ኤችፒ ፕሪንተር ብዛት 50፣ የምግብ ቤት ማሽን ብዛት

15፣ የተለያዩ የመኪና ጎማዎችና ስፐር ፓርቶች፣ እስፖንጅ ፍራሾች ብዛት 818፣ ማርቲ በጣሳ ብዛት 1702፣ ቁጥራቸዉ የማይታወቁ ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የጣዉላ ሎከሮች እና የተለያዩ ብረታ ብረቶች (ወደ ስቴዲዮም አከባቢ)፣ ሚክሲድ ፎሲት ብዛት 152፣ የብሉኬት ማፍጫ የብረት ብዛት 196 ያሉ በርካታ ንብረቶች ተከማችተው የተቀመጡ መሆናቸው፤ ታውቋል፡፡

7.1.2 ***ሥጋት፣***

ዩኒቨርሲቲዉ የንብረት አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና አጠባበቅ በመመሪያው መሠረት ተፈፃሚ ካልሆነ በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ ይችላል፡፡

7.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

የዩንቨርሲቲውን ንብረት ከጥፋትና ከብክነት ለመከላከል ይቻል ዘንድ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ከላይ በተዘረዘሩት የቁጥጥር ድክመቶችና የአሰራር ክፍተቶች ላይ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

7.1.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

የሥራ አመራሩ፣

1. ንብረቶችን በካይዘን ፍልስፍና በመመራት በስርዓት ለማስቀመጥ መሞከሩን፤ ሆኖም ግን አሁን ላይ ያሉት እቃ ግምጃ ቤቶች የዩኒቨርሲቲዉን እድገት ባላገናዘበ መልኩ ቀደም ሲል የተሰሩና አሁን ሪፈራል ሆስፒታሉን ጨምሮ ላሉአቸው /6/ ስድስት ግቢዎች አገልግሎት የሚሰጡ በመሆኑ የመጋዝን ጥበት ስላለ የተፈጠረ ችግር መሆኑንና ይህን ለመፍታት ተጨማሪ መጋዝኖች በአፄ ፋሲል፤ በማራኪ እና በመለስ ዜናዊ ግቢዎች በመገንባት ላይ በመሆናቸዉ የመጋዘኖች ግንባታ ሲጠናቀቅ ችግሩ ይፈታል የሚል እምነት እንዳላቸው፣
2. በቋሚ እቃዎች እቃ ግምጃ ቤት የዋጋ ግምታቸዉ የማይታወቅ ከcentere for international Unique in Ethiopia የህክምና እቃዎች አሉ ለተባለዉ ትክክል ነዉ ፤ ይሁን እንጂ እቃዎች በተለያየ ጊዜ በእርዳታ፤ በስጦታ እና ከምርምር ተርፈዉ የተመለሱ ቢሆንም በወቅቱ የዋጋ መረጃ ባለመኖሩ ዋጋቸዉ ሳይሞላ መቅረቱን፣ ይሁንና አሁን ባለዉ የገበያ ዋጋ ግምታቸዉን አጥንተው የሚመዘግቡ መሆኑን፣

3. በቋሚ እቃዎች እቃ ግምጃ ቤት ከተገዙ ጀምሮ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ አዳዲስ ንብረቶች አሉ ለተባለዉ ኮንፈረንስ ጠረጴዛዎች ለሪፈራል ሆስፒታል የተገዙ ሲሆን የተወሰኑ ህንፃዎች ባለመጠናቀቃቸዉ በመጋዝን ዉስጥ እንዲቆዩ የተደረገ እንጂ በትርፍነት የተቀመጠ አለመሆኑን፤ በመጋዝን ዉስጥ አሉ የተባሉት ካዝናዎች ሆስፒታሉ ለሚያሰራቸዉ የእለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች ቁጥር እጨመረ በመምጣቱ ለዚህ አገልግሎት ወጭ እየሆነ የሚሰጡ መሆኑን፤ ሲፓፕ ማሽንና ኢንፋንት ራዲተር፤ ኢንኩቬተር እና ዌይት ስኬል በተመለከተ አሁን ተጠቃሚዎች እየወሰዷቸዉ መሆኑን፤ የተለያዩ ሰሌዳዎች በመጋዝን ዉስጥ መኖራቸዉ ትክክል ሲሆን ነገር ግን ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ የሆነዉ በየትምህርት ክፍሎቹ በመማሪያ ክፍል ዉስጥ ስማርት ቦርድ በመገጠሙ እና በመተካቱ ምክንያት ያሉ ቢሆንም በቀጣይ ለተጠቃሚ ሌሎች ተቋማት የሚሰጡና እንዳስፈላጊነቱም ሌሎች እርምጃዎች የሚወሰዱባቸው እንደሚሆን፣ የመሪ ዘይት አለ ለተባለዉ በያዝነዉ የበጀት ዓመት ይህነን ታሳቢ በማድረግ በእቃ ግምጃ ቤት ያለዉ የሞተር ዘይት እንዳይገዛ ክትትል እያደረጉ መሆኑን፣ አሉ የተባሉት የቧንቧ እቃዎችን በተመለከተ በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ግቢዎች ከሚደረጉ የግንባታ ማስፋፊያ ስራዎች ጋር በተያያዘ እቃዎች እየታዩ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ የሚደረግ መሆኑን፣
4. በአላቂ እቃዎች ግምጃ ቤት ለበርካታ ዓመታት ወጭ ሆነዉ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የፕሪንተር እና የፎቶ ኮፒ ቀለሞች፤ ላርጎ ሳሙና እና የተለያዩ የደንብ ልብሶች አሉ ለተባለዉ የፕሪንተር እና ፎቶ ኮፒ ቀለሞች ብክነት እንዳይፈጠር በየሩብ ዓመቱ ለሁሉም ስራ ክፍሎች ለማከፋፈል ተቀመጠ እንጂ በትርፍነት የተቀመጠ አለመሆኑን፣ የደንብ ልብሶችም ለሰራተኛዉ እየታደለ ያለ መሆኑ እና በሆስፒታሉ ለተለያዩ የኦፕሬሽን ስራዎች እና ለህሙማን መኝታ አገልግሎት በየጊዜዉ እየወጡ ጥቅም ላይ የሚዉሉ መሆኑን፤ ላርጎ ሳሙናም በተመሳሳይ ብክነት እንዳይፈጠር በየሩብ ዓመቱ ለሁሉም ስራ ክፍሎች ለማከፋፈል ተቀመጠ እንጂ በትርፍነት የተቀመጠ አለመሆኑን፣
5. በቋሚ እቃዎች እቃ ግምጃ ቤት አሲድ መያዝና አለመያዛቸዉ ያልታወቁ ሲሊንደሮች ለዓመታት ተቀምጠዉ መገኘታቸዉ ለተባለዉ የዘርፉ ባለሙያ /የባዮ-ሜዲካል ክፍል / እንዲያያቸዉ ተደርጎ ቀጣይ ስራ ላይ እንዲዉሉ እንደሚደረግ፣

6. አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ንብረቶች በሚወገዱ ንብረቶች እቃ ግምጃ ቤት መኖራቸዉ ለተባለዉ ንብረቶችን ለማስወገድ ለሚመለከታቸዉ አካላት መግለጫ አቅርበው እና አስወጋጅ ኮሚቴ አቋቁመው በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኙ፣

ለሥራ አመራር ደብዳቤው በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

7.2 <u>ተሽከርካሪ መኪናዎች፣</u>

7.2.1 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ስለሌላቸው ተሽከርካሪ መኪናዎች፣</u>

7.2.1.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ዓ.ም ክፍል ሁለት አንቀፅ 6/1 የመንግሥት መ/ቤት በግዥ፣ በስጦታ፣ በዝውውር...ወዘተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ መኪና የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ ቢያንስ መሠረታዊ መረጃዎችን መዝግቦ መያዝ እንዳለበት ይገላፃል፡፡

የዚሁ መመሪያ ክፍል 3 አንቀጽ 9/1 እና 2 ደግሞ መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተል እና መዝግቦ ለመያዝ እንዲረዳቸው የተሽከርካሪዎች የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸውና እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች በዚህ መሠረት መያዛቸው ሲጣራ፣

ተ.ቁ	የተሽከርካሪው ዓይነት	ሠሌዳ ቁጥር	የጌጅ እና ሊብሬ ሁኔታ	የተገዛበት ዓ.ም
1	ፎርድ ፒክ አፕ	ኢ.ት-4-08651	ጌጁ የማይሰራ	2002
2	ፍላት 682 ኤነትሬ	ኢ.ት-4-09494	ጌጁ የማይሰራ	1980
3	ዳዎ ሂቪ ትራክር	ኢ.ት-4-10860	ጌጁ የማይሰራ	2006
4	ፍላት 682 ትራክር	አማ-4-01115	ጌጁ የማይሰራ	1988
5	ማዝዳ ደብል ፒክ አፕ	ኢ.ት-4-18577	ሊብሬ የሌለው	2006
6	ቶዮታ	ኢ.ት-4-19993	ሊብሬ የሌለው	2007
7	ቶዮታ	ኢ.ት-4-20495	ሊብሬ የሌለው	2007
8	ቶዮታ	ኢ.ት-4-21305	ሊብሬ የሌለው	2007

- 4 የተለያዩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መከታተያ የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ የማይሰራ መሆኑና ተሽከርካሪዎቹ በሂዱበት ኪ/ሜ ተገምቶ ነዳጅ የሚሞላላቸው መሆኑ፣
- 4 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

7.2.1.2 <u>ስጋት</u>

- ጌጅ የሌላቸው ተሽከርካሪዎችን የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ለመቆጣጠር ስለማያስችል ለነዳጅ ብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- የተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ያለመኖር ተሽከርካሪዎቹ ትክክለኛ የመንግስት ንብረት መሆናቸውን ላያሳይ /የባለቤትነት ጥያቄ ሊያስነሳ/ ይችላል፡፡

7.2.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- ጌጃቸው የተበላሹ ተሽከርካሪዎች ለምንና እንዴት እንደተበላሹ ተጣርቶ ሊጠገን ወይም ሊቀየርላቸው የሚገባ ሲሆን የነዳጅ እደላ ሥርዓቱም አንድ ተሽከርካሪ በሊትር በአማካይ በሚጓዘው ርቀት መጠን እየተለካ መሰጠት ይገባል፡፡
- የተሽከርካሪዎች የተሟላ የህይወት ታሪክ የሚገልጽ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ለሌላቸውም ሊወጣ ወይም ቀደም ሲል ወጥቶ ከሆነ ተፈልጎ ማስረጃው በተገቢው ቦታ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

7.2.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

- ጌጃቸው ከማይሰራው ውስጥ 2 ተሽከርካሪዎች ከ3 ዓመት በላይ በመለዋወጫ እጥረት ምክንያት የቆሙ እና ወደፊት ቢጠገኑ እንዲሰራ የሚደረጉ ሲሆን ሌሎች 2 ተሽከርካሪዎች ደግሞ አሁን በሥራ ላይ ያሉ በመሆኑና እንደተባለው ጌጃቸው በሥራ ላይ እያሉ የተበላሹ በመሆኑ ተጠግነዉ አገልግሎት እንዲሰጡ እንደሚደረግ፣
- ሊብሬ የሌላቸው 4 ተሽከርካሪዎች ሊብሬያቸዉን ግዥዉን ከፈጸመዉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በመጠየቅ እና በማምጣት በፋይላቸዉ እንዲያያዝ እንደሚደረግ፣

በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

8. ልዩ ልዩ፣

8.1 የውስጥ ኦዲት ክፍል በሰው ኃይል ያልተሟላ ስለመሆኑ፣

8.1.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች የማደራጀትና በቂ የትምህርት ዝግጅትና አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያካበተ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ የመመደብ የመ/ቤት የበላይ ኃላፊ ኃላፊነት እንደሆነ ይገልፃል፡፡

በዚህ መሠረት የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በሚፈለገው የሰው ኃይል መሟላቱ ሲጣራ፣ በመዋቅሩ መሠረት ለክፍሉ በአጠቃላይ 22 ኦዲተሮች የሚያስፈልግ ሲሆን አሁን ያለው የሰው ኃይል አስራ ሶስት (13) ባለሙያዎች ብቻ በመሆኑ ከክፍሉ የሰው ሀይል መዋቅር ጋር ሲነፃፀር ዘጠኝ (9) ክፍት የሥራ መደብ ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

8.1.2 ስጋት

- የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በበቂ የሰው ኃይል ካልተደራጀ በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አተገባበር ላይ የሚደረገው ክትትል በቂ ላይሆን ይችላል፡፡

8.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

- ክፍሉ አግባብነት ባለው የሰው ኃይል በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት፣ ወይም በዝውውር እንዲሟላ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

8.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ፣

- የዉስጥ ኦዲተሮችን የሰዉ ሃይል ማሟላትን በተመለከተ በዉስጥ ኦዲተሮች አስተዳደር መመሪያ መሠረት የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ዉክልና ካልሰጠ በስተቀር በራሱ የሚሟላ በመሆኑ ዩኒቨርሲዉ በራሱ የሠዉ ሃይሉን ለማሟላት ያልቻለ ሲሆን በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በኩል ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ ዉክልና ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሰዉ ሃይሉን ለማሟላት ጥረት የተደረገ ሲሆን፣ ከዩኒቨርሲቲዉ በደረጃ ዕድገት፣ በዝዉዉር ለማሟላት መመሪያው ስለማይፈቅድ በአብዛኛዉ ክፍት መደቦችን በቅጥር እንዲሟሉ ወደ ዉጭ በማዉጣት በቅጥር ለማሟላት ጥረት የተደረገ ቢሆንም መስፈርቱን አሟልተዉ ለኦዲት ለመቀጠር በቂ የሠዉ ሃይል ከገበያ ማግኘት ስላልተቻለ እና ቅጥሩም ከተከናወነ በኋላ በገንዘብና

ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መጽደቅ የሚገባዉ በመሆኑ በተፈለገዉ ፍጥነት ለማሟላት አለመቻሉን ጠቅሰው በአሁኑ ሰዓት 3 ተጨማሪ የሰዉ ሃይል በመቀጠሩ ቀደም ሲል የነበረዉ ክፍት 9 ወደ 6 ክፍት መደብ ዝቅ ያለ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

9. <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች፣</u>

9.1 <u>ግኝት፣</u>

- በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(በ) መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በውጭ ኦዲት ወይም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡
- በተጨማሪም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰርት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና እርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የጎንደር ዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፣

<u>የ2008 በጀት ዓመት</u>

- ግላሚንድ ፋርማ ትሬዲንግ መድሐኒትና የህክምና መሳሪያዎች ጅምላ አከፋፋይ ለዩኒቨርሲቲው ሪፌራል ሆስፒታልና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድሃኒቶች፣ ሬኤጀንቶች፣ ኬሚካሎች እና መሳሪያዎች በተፈረመው ውል መሰረት የ30 ቀን የጊዜ ገደብ የተሰጠው ሲሆን ንብረቱን በወቅቱ ገቢ ባለማድረጉ በድምሩ ከአቅራቢዉ ላይ ብር 24,135.10 የጉዳት ካሳ ቅጣት ለዩኒቨርሲቲው ገቢ መደረግ ሲገባ ሳይደረግ መገኘቱ፣
- የሥራ አመራር ካውንስል በወሰናቸው የተለያዩ ውሳኔዎች መሠረት፣ በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከሚያስተምሩ እንግዳ መምህራን ጋር ቀጥታ በሚያስተምሩት ሰዓት

/direct working contact hours/ በየወሩ ውል በመያዝ በመመሪያ ከተፈቀደው ውጪ፣ በናሙና ኦዲት ከተደረገው ሂሳብ ውስጥ ለትርፍ ሰዓት ክፍያ በክሬዲት አዎር የተፈቀደውን የክፍያ ተመን ባስተማሩበት ሰዓት (Contact hour) በማባዛት

- በሪፈራል ሆስፒታልና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በድምሩ ብር 947,440.00፣
- በመለስ ግቢ ግብርና ኮሌጅ ለአንድ እንግዳ መምህር ብር 18,000.00፣
- በአፄ ፋሲል ግቢ ከአንድ ለእንግዳ መምህር ብር 11,200.00

በድምሩ ብር **976,640.00** ለትርፍ ሰዓት /over load payment/ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ማሰራት ሲገባ ይህ ሳይሆን መከፈሉ፣

- በአጠቃላይ ድምር ብር **790,768.81** ገንዘቡ መከፈሉን የሚያረጋግጥ የሽያጭ ደረሰኝ **(cash sales invoice)** ማስረጃ ሳይቀርብለት በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (credit sales invoice) ብቻ በወጪ መመዝገቡ፣
- **በአፄ ቴዎድሮስ ግቢ** ለጃን ተከል ማተሚያ ቤት ለተከፈለ ብር 15,525.00 የህትመት ወጪቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ሞ/19 የሌለ መሆኑ፤ **በማራኪ ግቢ** ለመስተንግዶ ለተከፈለው ክፍያ ብር **40,834.57** ግብዣዉ እንዲከናወን የፈቀደዉ አካል፤ የተጋባዦች ማንነትና ብዛት እንዲሁም ስለመሳተፋቸዉ የሚያሳይ የሰአት ፊርማ ባለመቅረቡ የክፍያዉን ህጋዊነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

  በአጠቃላይ ድምር ብር **56,359.57 በ2ቱ ግቢዎች** ለወጣው ወጪ የተሟላ ማስረጃ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በአጠቃላይ ድምር ብር 1,367,182.26 ለለውጥ ሥራ የተከፈለ ቢሆንም የለውጥ ስራ ትዕዛዙ ያስፈለገበት ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በየደረጃው የተያዙና የጸደቁ ማስረጃዎች ለኦዲት ያልቀረቡ ሲሆን ለቫሪኤሽን ኦርደር በሚል በውል ከተያዘው በላይ ብር 5,544,701.61 መወራረዱ፣

<u>**የ2007 በጀት ዓመት**</u>

- ዩኒቨርሲቲው ለገቢ ማመንጫነት ያቋቋማቸው ጃንተከል ማተሚያ እና ብሩህ ሆቴል ልዩ ልዩ ስራ መተዳደሪያ ደንቦችና መመሪያዎች በቦርድ መጽደቅ ቢገባም ያልፀደቀ መሆኑ፣

የ2006 በጀት ዓመት

- አለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 310,320.0 ተመለሻ መሆን ሲገባው ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ለICT እና ምህንድስና ባለሙያ ሰራተኞች ማትጊያ መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ ከተመን በላይ በድምሩ ብር 94,000 ክፍያ የተፈፀመ እና መመለስ የሚገባው ገንዘብ ተመላሽ አለመደረጉ፣
- ከዩኒቨርሰቲው የውስጥ ገቢ ለመምህራን ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈከለ የቤት አበልና የኃላፊነት አበል ክፍያ ብር 1,234,064.35 ተመላሽ መሆን ሲገባው ተመላሻ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ለተለያዩ የኮሚቴ አባላት ለእያንዳንዳቸው ብር 5,000.00 እንዲሁም ለሁለት የኮሚቴ አባላት ለእያንዳንዳቸው ብር 2,500.00፣ በድምሩ ብር 35,000.00፣ ለንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ አባላት ብር 29,100.00፣ በጠቅላላው ብር 64,100.00 ያለአግባብ የተከፈለ የማበረታቻ ክፍያ ተመላሽ መሆን ሲገባ ተመላሽ አለመደረጉ፣

9.2 ስጋት፣

በኦዲት ግኝቶች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ፡-

- ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜን ለኪሳራ ሊዳርግ የሚችል ነው፡፡
- ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋትና መጉደል መንገድ የሚከፍት አሠራር በመሆኑ ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በሕግ፤ በደንብና መመሪያ ላይ በመመስረት የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶችን ሥራ ላይ አለማዋል የተሻለ አሠራርን መከተል አያስችልም፡፡

9.3 **የማሻሻያ ሃሳብ፤**

- የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜ የወጣባቸው በመሆኑ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሥራ አመራሩ፣ የዩኒቨርስቲው ቦርድና የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

9.4 <u>**የስራ አመራሩ ምላሽ፣**</u>

<u>የ2008 በጀት ዓመትን በተመለከተ</u>

- **የኦቨር ሎድ ክፍያ-** ጉዳዩ መፍትሄ እንዲሰጠዉ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ሚ/ር እና ለትምህርት ሚኒቴር በሕግ ማዕቀፍ ያልተጠቃለሉ የክፍያ አይቶችን በመዘርዘር ክፍያዎች እንዲፈቀዱ ጥያቄ ማቅረባቸውን፣
- **የክብር** (Honorarium) **ክፍያ እና የመመረቂያ ጽሁፍ ለገመገሙ መምህራ የተፈጸመ ክፍያ-**ጉዳዩ መፍትሄ እንዲሰጠዉ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ሚ/ር እና ለትምህርት ሚኒቴር በሕግ ማዕቀፍ ያልተጠቃለሉ የክፍያ አይቶችን በመዘርዘር ክፍያዎች እንዲፈቀዱ ጥያቄ ማቅረባቸውን፣
- **የሽያጭ ደረሰኝ ሳይቀርብለት በዱቤ ደረሰኝ የተፈጸመ ግዥ-**ደረሰኞችን ለማሰባሰብ ጥረት መደረጉን፣
- **የተሟላ ደረሰኝ ያልቀረበላቸዉ ክፍያዎች-**በዩኒቨርሲቲዉ በኩል ደረሰኝ እንዲቀርቡ ደብዳቤ የተጻፈ ሲሆን እስካሁን ደረሰኞች ሊቀርቡ አለመቻሉን፣
- **የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበላቸዉ ክፍያዎች-**በጃንተከል ማተሚያ ቤት ለምርምር አገልግሎት የታተመ የቤተሰብ መጠይቅ በወቅቱ ወደ ዕቃ ግምጃቤት ገብቶ እና ተመራማሪዎ ወጭ በማድረግ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑን፣ እየገለጽን ለማስረጃም፡-

<u>የ2007 በጀት ዓመትን በተመለከተ</u>

- የገቢ ማመንጫ ተቋማት መተዳደሪያ ደንቦች በቦርድ ማስጸደቅን በተመለከተ በቦርድ አጀንዳ እንዲቀርብ መጠየቁን፣

<u>የ2006 በጀት ዓመትን በተመለከተ</u>

- በፐብሊክ ሰርቪስ ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ-ክፍያዎች አስተያየት ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ መቋረጣቸውን፣ ተመላሽ ለማድረግ ግን ሠራተኞች በትርፍ ሰዓት

- ገብተዉ የሠሩበት ስለሆነ እና አገልግሎቱ ስለተሰጠ፣ መምህራንም ዉል ገብተዉ አገልግሎት የሰጡበት ስለሆነ፣ ኮሚቴዎችም ለሰጡት መልካም አገልግሎት የተፈጸመ ክፍያ በመሆኑ ክፍያዉን ማስመለስ የሥራ ተነሳሽነትን ስሚጎዳ ማስመለስ አለመቻሉን፣

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

2009

			የህንድ ሀገር መምህራን ደመወዝ ላይ የሥራ ግብር ያልተቀነሰ ስለመሆኑ፣										
No.	የተቀጠሩበት ጊዜ	ሐምሌ 2008	ነሐሴ 2008	መስከረም 2009	ጥቅምት 2009	ህዳር 2009	ታህሳስ 2009	ጥር 2009	የካቲት 2009	መጋቢት 2009	ሚያዚያ 2009	ግንቦት 2009	ሰኔ 2009
Dr.Pujari Kr	**April,10/2012**	59,388.61	59,388.61	60,604.34	61,198.19	61,198.19	61,198.19	62,266.56	62,266.56	62,266.56	63,152.06	63,152.06	63,152.06
Dr.Sanjay si	**April.1,2015**	42,802.60	42802.60	43,678.80	44,106.80	44,106.80	58,992.85	60,022.72	60,022.72	60,022.72	60,876.31	60,876.31	60,876.31
Dr.Raja Nag	**June,24,2010**	58,853.58	58,853.58	60,058.35	60,646.85	60,646.85	60,646.85	61,705.60	61,705.60	61,705.60	62,583.13	62,583.13	68,272.50
Dr.Kurma S	**Nov,10,2010**	59,388.61	59,388.61	60,604.34	61,198.19	61,198.19	61,198.19	62,266.56	62,266.56	62,266.56	63,152.06	63,152.06	63,152.06
Dr. C. Subra	**Nov,10,2010**	58,853.58	58,853.58	60,058.35	60,646.85	60,646.85	60,646.85	61,705.60	61,705.60	61,705.60	62,583.13	62,583.13	62,583.13
Dr.Deepak	**Nov,20,2010**	58,853.58	58,853.58	60,058.35	60,646.85	60,646.85	60,646.85	61,705.60	61,705.60	61,705.60	62,583.13	62,583.13	62,583.13
Dr.Haidarul	**Oct,1,2012**	42,802.60	42802.60	43,678.80	44,106.80	44,106.80	44,106.80	44,876.80	44,876.80	44,876.80	45,515.00	45,515.00	45,515.00
Mr.G.B.Mu	**oct,15,2014**	42,802.60	42802.60	43,678.80	44,106.80	44,106.80	44,106.80	44,876.80	44,876.80	44,876.80	45,515.00	45,515.00	45,515.00
Mr.Saravan	**oct,15,2014**	44,407.70	44,407.70	45,316.76	45,760.81	45,760.81	45,760.81	46,559.68	46,559.68	46,559.68	47,221.81	47,221.81	47,221.81
Mr.Babar Ja	**oct,15,2014**	44,407.70	44,407.70	45,316.76	45,760.81	45,760.81	45,760.81	46,559.68	46,559.68	46,559.68	47,221.81	47,221.81	47,221.81
Dr.Anis Mil	**oct,15,2014**	44,407.70	44,407.70	45,316.76	45,760.81	45,760.81	45,760.81	46,559.68	46,559.68	46,559.68	47,221.81	47,221.81	47,221.81
Mr.Anand A	**oct,15,2014**	44,407.70	44,407.70	45,316.76	45,760.81	45,760.81	45,760.81	46,559.68	46,559.68	46,559.68	47,221.81	47,221.81	47,221.81
Prof.Koppa	**Oct,15,2014**	48,687.96	48,687.96	49,684.64	61,198.19	61,198.19	61,198.19	62,266.56	62,266.56	62,266.56	63,152.06	63,152.06	63,152.06
Dr.Puvvada	**oct,15,2014**	48,687.96	49,684.64	49,684.64	50,171.49	50,171.49	50,171.49	51,047.36	51,047.36	51,047.36	51,773.31	51,773.31	51,773.31
Dr.Mokula	**Oct,15,2014**	37,987.31	37,987.31	38,764.94	39,144.79	39,144.79	39,144.79	39,828.16	39,828.16	39,828.16	40,394.56	40,394.56	40,394.56
Dr.A.V.Moh	**Oct,15,2014**	44,407.70	44,407.70	45,316.76	45,760.81	45,760.81	50,171.49	51,047.36	51,047.36	51,047.36	51,773.31	51,773.31	51,773.31
Dr. Mahalak	**Oct,15,2014**	52,968.22	52,968.22	54,052.52	54,582.17	54,582.17	54,582.17	55,535.04	55,535.04	55,535.04	56,324.81	56,324.81	56,324.81
Prof.Shams	**15,oct,2014**	70,089.26	70,089.26	71,524.04	72,224.89	72,224.89	72,224.89	73,485.76	73,485.76	73,485.76	74,530.81	74,530.81	74,530.81
Mr..Md.Asi	**oct,20,2014**	-	-	-	-	45,760.81	45,760.81	46,559.68	46,559.68	46,559.68	47,221.81	47,221.81	47,221.81
Mr.Sathyan	**Oct,29,2010**	47,082.86	47,082.86	48,046.68	48,517.48	48,517.48	48,517.48	49,364.48	49,364.48	49,364.48	50,066.50	50,066.50	50,066.50
Dr.K.Subrar	**Octo,15,2014**	37,987.31	37,987.31	38,764.94	39,144.79	39,144.79	39,144.79	39,828.16	39,828.16	39,828.16	40,394.56	40,394.56	40,394.56
Prof.Varghe	**sep, 25,2014**	51,363.12	51,363.12	52,414.56	61,198.19	61,198.19	61,198.19	62,266.56	62,266.56	62,266.56	63,152.06	63,152.06	63,152.06
Dr.Azamal	**sep,1,2010**	58,853.58	58,853.58	60,058.35	60,646.85	60,646.85	60,646.85	61,705.60	61,705.60	61,705.60	62,583.13	62,583.13	47,221.81
Prof.V.Ram	**Sep,11,2012**	64,203.90	64,203.90	64,518.20	66,160.20	66,160.20	66,160.20	76,290.56	76,290.56	76,290.56	77,375.50	77,375.50	77,375.50
Dr.Jothima	**Sep,12,2014**	37,452.28	37,452.28	38,218.95	38,593.45	38,593.45	38,593.45	39,267.20	39,267.20	39,267.20	39,825.63	39,825.63	39,825.63
Mrs.Shaik S	**sep,20,2010**	50,293.06	50,293.06	51,322.59	51,825.49	51,825.49	51,825.49	52,730.24	730.52730.2424	52,730.24	53,480.13	53,480.13	53,480.13
Mr.Moham	**sep,29,2010**	43,872.67	43,872.67	44,770.77	45,209.47	45,209.47	45,209.47	45,998.72	45,998.72	45,998.72	46,652.88	46,652.88	46,652.88
Dr.Kavitha	**Spet.11,2014**	42,802.60	42,802.60	43,678.80	44,106.80	29,772.09	58,992.85	60,022.72	60,022.72	60,022.72	60,876.31	60,876.31	60,876.31
ድምር		**1,338,116.31**	**1,210,705.20**	**1,364,508.55**	**1,398,185.63**	**1,429,611.73**	**1,478,129.22**	**1,512,909.12**	**1,460,178.88**	**1,512,909.12**	**1,534,424.43**	**1,534,424.43**	**1,524,752.48**
ያልተቆረጠ ታክስ		**468,340.71**	**423,746.82**	**477,577.99**	**489,364.97**	**500,364.11**	**517,345.23**	**529,518.19**	**511,062.61**	**529,518.19**	**537,048.55**	**537,048.55**	**533,663.37**

ድምር	**17,298,855.10**
ያልተቆረጠ ታክስ	**6,054,599.28**

አባሪ ቁጥር 3

የወጪ የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ በጀት	ልዩነት	ልዩነት በ % (ላልተሠራበት በጀት)
ከበጀት በላይ የወጣ መደበኛ በጀት				
6113	1,539,081.00	1,558,320.44	19,239.44	
6114	20,770,918.00	21,433,758.17	662,840.17	
6116	55,915,522.00	58,969,344.33	3,053,822.33	
6211	14,872,084.00	15,839,388.55	967,304.55	
6216	119,671,900.00	121,328,354.67	1,656,454.67	
6233	10,106,297.00	10,165,475.00	59,178.00	
6251	2,985,975.00	3,379,855.63	393,880.63	
6256	7,801,158.72	8,196,706.38	395,547.66	
6271	15,953,948.00	16,672,243.47	718,295.47	
6417	19,805,740.00	20,155,541.70	349,801.70	
		ድምር	**8,276,364.62**	
ሥራ ላይ ያልዋለ መደበኛ በጀት				
6133	121,891.00	54,760.89	67,130.11	55.07
6213	4,656,448.00	3,426,861.34	1,229,586.66	26.41
6217	8,916,988.00	7,914,465.23	1,002,522.77	11.24
6218	11,818,250.00	10,373,092.62	1,445,157.38	12.23
6219	2,573,597.00	2,015,885.69	557,711.31	21.67
6222	520,840.00	168,736.28	352,103.72	
6241	7,994,612.00	6,583,661.49	1,410,950.51	17.65
6243	1,615,000.00	787,259.28	827,740.72	51.25
6244	11,028,884.00	9,920,379.89	1,108,504.11	10.05
6253	3,592,736.00	2,087,215.76	1,505,520.24	41.90
6255	1,752,329.00	1,221,646.19	530,682.81	30.28
6257	6,390,940.00	4,990,222.95	1,400,717.05	21.92
6258	15,436,096.00	13,584,063.91	1,852,032.09	12.00
6259	7,090,200.00	5,805,408.66	1,284,791.34	18.12
6313	5,808,503.28	4,326,599.35	1,481,903.93	25.51
6314	2,774,894.00	1,954,058.49	820,835.51	29.58
		ድምር	**16,877,890.20**	
ከበጀት በላይ የወጣ ካፒታል በጀት				
6231	3,600,000.00	3,937,902.98	**337,902.98**	

<u>አባሪ ቁጥር 4</u>

የሚከናወነው ፕሮጀክት ዓይነት	Site	ፕሮጀክቱን የሚያከናውነው ድርጅት /ስም/	በመነሻ ውል መሠረት የተገባ የውል መጠን /ገንዘብ/	በውል መሠረት ግንባታው የተጀመረበት ጊዜ	በውል መሠረት ግንባታው የሚጠናቀቅበት ጊዜ	እስከ 2009 ዓ/ም ሰኔ ወር ድረስ የዘገየ በቀናት	የፀደቀ የውል ማራዘሚያ	እስከ 2009 ዓ/ም ሰኔ 30 ድረስ የዘገየ በቀናት (የጸደቀው ቀን ሲቀነስ)	ተለዋጭ ስራ/Variation order/ ካለ የገንዘብ መጠን	ስራው ያለበት ደረጃ እስከ ሰኔ 30 2009 ዓ/ም (%)	እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ/ም የተሰራ ሥራ የገንዘብ መጠን (በብር)		እስከ ሰኔ 30 2009 ዓ/ም የተከፈለ የገንዘብ መጠን (በብር)
ሎት-19 ፐብሊክ ሄልዝ ግንባታ	ሆስፒታል ግቢ	ክራፍት ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር	33,189,817.35	10/08/07	23/04/09	368	181	187	486,143	69.2%	22,970,672.59		21,429,823.89
ሎት-A የተማሪዎች መኝታና የመምህራን ቢሮ	ወረታ ከተማ	አስማማው አለን ህ/ስራ/ተቋራጭ	15,316,961.09	10/10/08	10/09/09	21	0	21	-	56.0%	8,577,498.21		4,749,857.01
ሎት-B እስቶር	ፋሲል ግቢ	አባይ ደምሴ ህ/ስራ/ተቋራጭ	6,777,462.85	15/02/08	21/08/09	69	0	69	-	29.7%	2,012,228.72		-
ሎት-A እስቶር	ማራኪ እና ፀዳ ግቢ	ጀማል መሃመድ ህ/ስራ/ተቋራጭ	6,777,461.85	09/11/08	21/08/09	69	0	69		80.8%	5,474,833.68		1,355,492.57

አባሪ ቁጥር 2

ቀን	የሂሳብ ምዝገባ ማዝገፎ	ቫውቸር ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የብር መጠን
28/11/2008	JV	44127	6111	37,748.00
26/12/2008	JV	50922	6111	37,748.00
25/01/2009	JV	51014	6111	36,995.00
21/02/2009	JV	51215	6111	38,300.00
28/03/2009	JV	51292	6111	33,839.00
21/04/2009	JV	52088	6111	33,839.00
25/05/2009	JV	52145	6111	33,839.00
28/06/2009	JV	52233	6111	39,673.00
26/07/2009	JV	52441	6111	52,273.00
25/08/2009	JV	52545	6111	52,273.00
25/09/2009	JV	52556	6111	52,273.00
17/10/2009	JV	52597	6111	52,273.00
			ድምር	**501,073.00**
27/11/08	JV	47751	6111	15,231.00
28/12/08	JV	47771	6111	15,231.00
25/01/09	JV	47783	6111	15,231.00
26/2/09	JV	47803	6111	15,231.00
26/03/09	JV	47819	6111	13,926.00
22/04/09	JV	47857	6111	13,926.00
25/5/09	JV	47893	6111	15,231.00
28/6/09	JV	47976	6111	15,231.00
22/07/09	JV	47999	6111	23,100.00
26/08/09	JV	53707	6111	23,100.00
25/09/09	JV	48096	6111	22,765.34
19/10/09	JV	53830	6111	23,100.00
			ድምር	**211,303.34**
			ጠቅላላ ድምር	**712,376.34**